https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 16
ADDIS ABABA 27th December 2018

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፵፫/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የፌደራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………………ገጽ ፲ሺ፯፻፺

**Content**

Regulation No.443/2018

Federal Public Prosecutors' Administration Council of Ministers Regulation ………………………………………….Page 10790

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፫/፪ሺ፲፩

## ስለ ፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፫/ ፪ሺ፰ አንቀፅ ፳፩/፩/ በተደነገገው መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩.** **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የፌደራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፫/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.** **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፫/ ፪ሺ፰ ነው፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 443/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FEDERAL PUBLIC PROSECUTORS

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 21(1) of Federal Attorney General Establishment Proclamation No. 943/2016.

## PART ONE
## General Provisions

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Federal Public Prosecutors' Administration Council of Ministers Regulation No. 443/2018"

2. **Definition**

In this Regulation unless the context requiresotherwise;

1/ "Proclamation" means the Federal Attorney General Establishment Proclamation No. 943/2016;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me



፪/ "መንግሥት" ማለት የፌደራል መንግሥት ነው፤

፫/ "መሥሪያ ቤት" ማለት በአዋጁ የተቋቋመው የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ነው፤

፬/ "ዋና ጉባኤ ወይም ንዑስ ጉባኤ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፩) መሠረት የተቋቋመው የፌደራል ዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፻ መሠረት የተቋቋመው ንዑስ ጉባኤ ነው፤

፭/ "ደረጃ" ወይም "የሥራ ደረጃ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ሥር በተዘረዘረው መሠረት ዐቃብያነ ሕግ የተቀጠሩበት፣ የተመደቡበት ወይም የተሾሙበት ደረጃ ነው፤

፮/ "ደመወዝ" ማለት በዐቃብያነ ሕግ የደመወዝ ስኬል መሠረት ለአንድ የሥራ ደረጃ የተወሰነ መነሻ ደመወዝ እና በየደረጃው በየጊዜው የሚሠጥ የደመወዝ ጭማሪ ነው፤

፯/ "ሹመት" ማለት አንድ ዐቃቤ ሕግ ከነበረበት ደረጃ ከፍ ወደ አለ ደረጃ የሚያድግበት ነው፤

፰/ በአዋጁ ትርጉም የተሠጣቸው ቃላትና ሐረጎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፱/ በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ይጨምራል።

**፫.የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ ፦

፩/ ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣

፪/ ምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አንድ፣

፫/ ምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሁለት ፣

፬/ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ አንድ ፣

፭/ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ ሁለት፣

፮/ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ ሦስት፣

፯/ ዐቃቤ ሕግ ደረጃ አንድ፣

፰/ ዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሁለት፣

2/ "government" means the Federal Government;

3/ "office" means the office of the Federal Attorney General established by the Proclamation;

4/ " Higher Commission" or " Lower Commission" means Lower commissions established pursuant to Article 12 (1) of Federal Public Prosecutors Administration Council of the Proclamation and Article 103 of this Regulation, respectively;

5/ "grade" or "work grade" means grade of public prosecutor employment, assignment or appointment as prescribed under Article 3 of this Regulation;

6/ "salary" means a starting salary and periodic increment given for a specific work grade in accordance with the salary scale of the Federal public prosecutors;

7/ "appointment" means the assignment of a public prosecutor from one grade to a higher grade;

8/ words and phrases defined under the Proclamation shall be applicable to this Regulation;

9/ In this Regulation, expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Scope of Application**

This Regulation shall be applicable to the following employed, appointed or assigned public prosecutors:

1/ Assistant Attorney General;

2/ Deputy Assistant Attorney General One;

3/ Deputy Assistant Attorney General Two;

4/ Higher Public prosecutor One;

5/ Higher Public prosecutor Two;

6/ Higher Public prosecutor Three;

7/ Public prosecutor Grade One;

8/ Public prosecutor Grade Two;

https://chilot.me


፱/ ዐቃቤ ሕግ ደረጃ ሦስት ወይም

፲/ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ ፣

ሆኖ በተቀጠረ፣ በተሾመ ወይም በተመደበ ዐቃቤ ሕግ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ዐቃቤ ሕግ አመራረጥ፣ ቅጥርና ሹመት**

**፬.ለዐቃቤ ሕግነት የሚያበቁ ሁኔታዎች**

፩/ ስለ ዐቃቤ ሕግ ሹመት እና ውስጣዊ አስተዳደር በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሆኖ የሚቀጠር ወይም የሚሾም ፡-

ሀ) በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነና በኢትዮጵያ የሚኖር፣

ለ) የሕግ ትምሕርት እንዲያስተምር በመንግሥት እውቅና ከተሰጠው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ፡-

፩) በሕግ ትምህርት በዲግሪ ወይም

፪) በሕግ ትምህርት በዲግሪና ከዚያ በላይ የተመረቀ፣

ሐ) በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ፣ በፍትሐዊነቱና በሥነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣

መ) እድሜው ፳፫ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሆነ፣

ሠ) የፌደራል መንግሥቱን የሥራ ቋንቋ የሚችል እና

ረ) ለሥራ ደረጃው የተዘጋጀውን ፈተና ያለፈ መሆን አለበት።

፪/ በዚህ ደንብ ስለ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ደረጃ የሚቀጠር ወይም የሚሾም ዐቃቤ ሕግ ለደረጃው የተወሰነውን የመመዘኛ መሥፈርት ማለትም ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ እንዲሁም እንደ ሁኔታው ልዩ ስልጠና ማሟላት አለበት።

፫/ የሚከተሉት ከዐቃቤ ሕግነት ሙያ የሚከለክሉ ሁኔታዎች ናቸው ፡-

9/ Public prosecutor Grade Three; or

10/ Candidate Public prosecutor.

**PART TWO**

**Selection, Employment and Appointment of Public Prosecutors**

**4. Qualification for a Public Prosecutor**

1/ Without prejudice to the provisions of appointment and administration of public prosecutorin the Proclamation,any person to be employed or appointed as a public prosecutor shall:

a) be an Ethiopian citizen and live in Ethiopia;

b) (1) be a graduate in law with a degree; or,

(2) be a graduate in law with a degree or above; from a recognized higher educational institution by government for law education;

c) have distinguished himself by his diligence; loyalty,fairness and good moral character;

d) be 23 years of age or above;

e) be able to use the federal working language; and,

f) pass the entrance examination for the specified grade.

2/ Without prejudice to the provisions regarding candidate public prosecutors, any public prosecutor to be employed or appointed at any grade shall fulfill the requirementfor the grade namely, educational qualification andwork experience and, as appropriate, special training.

3/ The following conditions prohibitit from public prosecutor profession:

https://chilot.me


ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነትን መተው ወይም በሕግ መሠረት ማጣት፤

ለ) በፍርድ ቤት ውሳኔ ለጊዜው ወይም ለዘወትር ለሕዝብ አገልግሎት ሥራ እንዳይመረጥ መከልከል፤

ሐ) በፍርድ ሰሌዳ ላይ የተመዘገበ የወንጀል ቅጣት መኖር፤

መ) በሕክምና ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ የዐቃቤ ሕግነት ሥራን ለመሥራት የማያስችል ሕመም መኖር፤

**፭.ስለ ዐቃቤ ሕግ ምልመላና ቅጥር አፈፃፀም**

፩/ መሥሪያ ቤቱ የዐቃብያነ ሕግን ምልመላና ቅጥር ማስታወቂያ ከማውጣቱ አስቀድሞ ክፍት የሥራ ደረጃው በሥራ ላይ ባሉ ዐቃብያነ ሕግ በሹመት ሊያዝ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

፪/ የዐቃብያነ ሕግ ምልመላና ቅጥር ሲፈፀም በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት፣ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ወይም በሌላ ሁኔታ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

፫/ መሥሪያ ቤቱ አመልካቾች ስለሚመደቡባቸው ክፍት የሥራ ደረጃዎች ተስማሚ በሆነው መንገድ ለ፴ (ሠላሳ) ተከታታይ ቀናት ማስታወቅና ምዝገባ ማከናወን አለበት፤ የሚያወጣው ማስታወቂያም የተባለውን ክፍት የሥራ ቦታ አጭር መግለጫ፣ ተፈላጊ ችሎታ፣ የሥራ ደረጃ፣ የሚከፈለውን ደመወዝና ሌላም መሰል አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት።

፬/ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር የሚወዳደሩ አመልካቾች መሥሪያ ቤቱ ያዘጋጀውን የቅጥር ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ማቅረብ አለባቸው።

፭/ መሥሪያ ቤቱ በቀረበለት ማመልከቻ መሠረት የተጠየቀውን መስፈርት ያሟሉ አመልካቾችን በመፈተን ለሥራው ብቁ የሆኑትን እና ከተወዳዳሪዎች መካከል በአጠቃላይ ውጤት ብልጫ ያገኙትን አመልካቾች ይመርጣል።

a) leaving Ethiopian nationality or depriving in legal ground;

b) prohibition from public service temporarily or permanently by court decision;

c) registration ofcrime penalty record;

d) certified pain with medical certificate unable for public prosecution;

**5. Procedure for selection and employment ofPublic Prosecutors**

1/ The Office shall ensure the open vacancy isunabletooccupy by appointment for Public Prosecutor on duty before the notifications of selection and employment.

2/ There shall be no discrimination in filling vacanciesbecause of their ethnic origin, sex, religion,political outlook, disability, HIV/AIDS or any other ground.

3/ The Office shall notify in detail and in appropriatemanner vacancies available for 30 consecutive days and register for the assignment ofpublic prosecutor. The notice of vacancy shall contain a short description of the vacancy, requiredqualification, work grade, salary and any other appropriate information.

4/ Candidates applying to be employed as public prosecutorsshall fill the Office’s employment application form.

5/ The Office, based on the application forms, shallexamine the candidates who seem fit and shall selectthe one with the best results.

https://chilot.me


፮/ የፈተናው ይዘት በመሥሪያ ቤቱ ያለውን ወቅታዊ ፍላጎት፣ ዐቃብያነ ሕግ የሚቀጠሩበትን ክፍት የሥራ ደረጃ ልዩ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ተፈታኙ ለሚወዳደርበት ደረጃ የሚመጥን ጠቅላላ ችሎታ፣ እውቀትና ተሠጥኦ ያለው መሆኑን የሚመዝን መሆን አለበት፤ ፈተናው እንዳስፈላጊነቱ የቃል ወይም የጽሑፍ ጥያቄ በማድረግ ወይም ሁለቱን የፈተና ዓይነቶች በማጣመር ወይም የተግባር ፈተና ሊሆን ይችላል።]

፯/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም የዐቃብያነ ሕግ ቅጥርና ድልድል ሲፈጸም በውድድር ውጤታቸው እኩል ወይም ተቀራራቢ ሲሆኑ፡-

ሀ) አካል ጉዳተኞች፣

ለ) ሴት አመልካቾች

ሐ) በአንጻራዊ ሁኔታ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ አነስተኛ ተዋፅኦ ላላቸው ብሔረሰቦች እንደቅደም ተከተላቸው ቅድሚያ ይሠጣቸዋል።

፰/ በቅጥር ሂደቱ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ውጤቱ ከተገለጸበት ቀን አንስቶ በ፭ (አምስት)ተከታታይ የሥራ ቀን ቅሬታውን በጽሑፍ ለዋና ጉባዔው ማቅረብ ይችላል። ዋና ጉባኤውም ቅሬታውን መርምሮ በ ፲ (አሥር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ያቀርባል። ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉም የውሳኔ ሃሳቡ በቀረበለት ፭ (አምስት) ተከታታይ የሥራ ቀን ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል።

**፮.<u>ማስረጃ ስለማቅረብ</u>**

በመሥሪያ ቤቱ የሚቀጠር አዲስ ዐቃቤ ሕግ ከመቀጠሩ በፊት የሚከተሉትን ማስረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ አለበት ፡-

፩/ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ፣

፪/ የጤንነት ምርመራ ውጤት ፣

6/ The content of the examination shall take intoaccount the work progress of the Office and the special nature of the vacancy concerned to evaluatethe general knowledge, capability andthegift of the candidate. Where appropriate the examination may be oral or written or both or practical evaluation may be used.

7/ Notwithstanding the provisions of Sub- Articles (2) of this Article, in recruitment and deployment when there is equal or nearly equal result preference shall be given to:

a) candidates with disabilities;

b) female candidates;and

c) members of nationalities comparatively less represented in the Office,having equal or close scores to that othercandidates.

8/ Applicant aggrieved by the examination result, may appeal to the Higher Commission within 5 (five) consecutive working days from the date of notification; the Higher Commission after investigating the appeal shall give recommendation for the Attorney General within 10 (ten) consecutive working days. The Attorney General shall give decision within 5 days from the date of decision and the decision of the Attorney General shall be final.

**6. <u>Supporting Documents</u>**

A new employee in the Office shall submit thefollowing complete documents:

1/ educational qualification and work experience;

2/ health certificate;

https://chilot.me


፫/ ከወንጀል ቅጣት ነጻ ለመሆኑ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የተሰጠ ማረጋገጫና፤

፬/ ሌሎች በመሥሪያ ቤቱ የሚጠየቁ መሰል ማስረጃዎች።

**፯.ስለ ጤንነት ምርመራ**

፩/ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር ተወዳድሮ በመሥሪያ ቤቱ በእጩነት የተመረጠ አመልካች ለመቀጠር ኤች አይ ቪ/ኤድስን ሳይጨምር በቅድሚያ የጤና ምርመራ አድርጎ ማለፍ አለበት።

፪/ መሥሪያ ቤቱ ፡-

ሀ) በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር ተወዳድሮ በዕጩነት የተመረጠ አመልካች በጤና ረገድ ለሥራው ተስማሚ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብበትን የምርመራ ዓይነት ይወስናል፤

ለ) ተገቢውን የሕክምና ምርመራ በማድረግ የሕክምና ምስክር ወረቀት የሚሠጡ የሕክምና ተቋማትን ሊወስን ይችላል።

**፰.ስለ ሹመት አሠጣጥ መሠረታዊ መርሆዎች**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፪) እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የዐቃቤ ሕጉ የሥራ አፈፃፀም፣ ለአዲሱ ኃላፊነት ያለው በጎ ፈቃድ እና ያሳተመው የጥናትና ምርምር ሥራ ካለ ለሹመት አሠጣጥ መሠረት ናቸው።

፪/ ሹመት የሚሠጠው ለሥራው አስፈላጊ ሲሆን እና ክፍት የሥራ ደረጃ ሲኖር ብቻ ነው።

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭(፯) የተደነገገው ለሹመት አሠጣጥም ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

**፱.ስለዐቃቤያነ ሕግ አሿሿም**

፩/ ለረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግነትና ለምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግነት የታጩ ሰዎች በሚመለከተው ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ አቅራቢነት በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ይሾማሉ።

3/ police certificate for not involving in criminalactivities;

4/ other necessary documents requested by the Office.

**7. Medical Examination**

1/ A candidate who is selected to be employed in the Office as public prosecutor shall pass medical examination excluding HIV/AIDS.

2/ The Office:

a) shall determine the requirements ofmedical fitness having regard to the nature of thework;

b) may designate medical practitioners or institution to make such examinations.

**8. Basic Principles for Appointment**

1/ Without prejudice to the provisions of Article 11(2) of the Proclamation and Article 4 of this Regulation, printed studies and research, if there and interest for the new position of the public prosecutor are basic principles for appointment.

2/ An appointment shall be made only where it is necessary for the work grade and there is vacancy.

3/ Provisions stated under Article 5(7) of this Regulation shall be applicable to appointment as well.

**9. Appointment of Public Prosecutors**

1/ Assistant Attorney General and Deputy Assistant Attorney General shall be appointed by the Attorney General upon recommendation by the respective Deputy Attorney General.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ሥር ከተመለከቱት የሹመት ደረጃዎች በታች በሆነ ደረጃ ላይ የሚሾሙ ዐቃብያነ ሕግ በዋናው ጉባኤ አቅራቢነት በጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ይሾማሉ።

**፲. ቃለ መሐላ ስለመፈፀም**

፩/ ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ ዐቃቤ ሕግ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በዋና ጉባኤው ፊት ቀርቦ በዋና ጉባኤው ሰብሳቢ አማካኝነት የሚከተለውን ቃለ መሐላ መፈፀም አለበት፤

"እኔ………………………………………………ለሀገሬ ታማኝ በመሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን፣ ሌሎች ሕጎችን የኢትዮጵያን ዓለም ዓቀፍ ግዴታዎች ያለምንም ማመንታት ላከብርና ላስከብር፣ የፌደራል መንግሥት ሕጎችን በመፈጸምና በማስፈጸም የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ልሠራ፣ የሥራ ድርሻዬን ሕግ በሚደነግገው መሠረት በመፈጸም የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት ላከብርና ላስጠብቅ፣ የግል ጥቅም ሳልፈልግ ማንንም በመውደድ፣ በመጥላት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት አድሎ ላላደርግ፣ በሥራ ምክንያት ወይም በሌላ አጋጣሚ ያገኘሁትን ምሥጢር ከአገልግሎቴ መቋረጥ በኋላ እንኳን ቢሆን በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ላልገልጽ፣ በሥራዬም ሆነ በግል ሕይወቴ የሙያዬን ክብር ልጠብቅ፣ ማንኛውንም ተጽእኖ ሳልፈራ በሀቀኝነት፣ በቅንነትና በትጋት ሀላፊነቴን ለመወጣት ቃል እገባለሁ።"

፪/ ቃለ መሐላውን ለመፈፀም እንቢተኛ የሆነ ወይም በተዐቅቦ የፈፀመ አመልካች አይቀጠርም፤

፫/ ቃለ መሐላው በሥነ-ሥርዓቱ ላይ በተገኙ የዋና ጉባኤው አባላትና በመሐላ ፈጻሚው መፈረም ይኖርበታል፤

፬/ ቃለ መሐላው በዐቃቤ ሕጉ የግል ማሕደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት።

2/ Levels of Public Prosecutors appointment below Sub-Article (1) of this Article shall be appointed by the Attorney General upon recommendation by the Higher Commission.

**10. Oath**

1/ Any new employee of a public prosecutor shall, before assuming office, take the following oath before the Higher Commission with the chair person of the Higher Commission:

"I___________________________________solemnly wear that I shall be loyal to my country and pledge to abide by the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, other laws and Ethiopian international duties without any hesitation, to work for the supremacy of law, to execute and cause to implement laws, to carry out my responsibilities on the basis of the law, to respect human dignity and safeguard human right and that I shall discharge my duties honestly, sincerely, diligently and impartially without seeking personal gain and without fear or favor of any kind and not to disclose any information that is revealed to me by reason of my duties and is classified as confidential even after the termination of my service."

2/ Applicant who refused to make the oath or abstainer shall not be employed.

3/ The oath shall be signed by the members of Higher Commission attended the ceremony and the oath performer.

4/ The oath shall be kept in the personal file of the public prosecutor.

https://chilot.me


**፲፩.ስለዐቃቤ ሕግ ቅጥርና ሹመት መሠረዝ**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በዐቃቤ ሕግነት ለመቀጠር ወይም ለመሾም የሐሰት ማስረጃዎችን ካቀረበ ቅጥሩ ወይም ሹመቱ በማናቸውም ጊዜ ይሠረዛል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ቅጥሩ ወይም ሹመቱ የተሰረዘበት አቃቤ ሕግ ቅጥሩ ወይም ሹመቱ ከመሠረዙ በፊት የተከፈለውን ደመወዝና ሌላ ጥቅማ ጥቅም እንዲመልስ መደረግ አለበት።

**፲፪.ስለሙከራ ጊዜ**

፩/ የዕጩ ዐቃቤ ሕግ የሙከራ ጊዜ ለ ፮ (ስድስት) ወር ሆኖ የሥራ አፈጻጸም ውጤቱ ከመካከለኛ በታች ከሆነ የሙከራ ጊዜው ለተጨማሪ ፫ (ሦስት) ወር ሊራዘም ይችላል፤

፪/ ዕጩ ዐቃቤ ሕጉ በተራዘመው የሙከራ ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ምዘና ውጤት ካላገኘ ከሥራ ይሰናበታል፣

፫/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪(፭) እና (፮) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሙከራ ላይ ያለ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ ከሥራ በመጣ ሕመም ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ያልጨረሰውን የሙከራ ጊዜ ከሕመሙ ወይም ከጉዳቱ ከዳነበት ጊዜ አንስቶ እንዲጨርስ ይደረጋል፤

፬/ በሙከራ ላይ የሚገኝ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአንድ ወር በታች በሥራው ላይ ካልተገኘ በሥራው ላይ የተገኘበት ጊዜ ብቻ ታስቦ የሥራ አፈፃፀም ይሞላለታል፤

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ ቢኖርም በወሊድ ምክንያት ከአንድ ወር በላይ በመደበኛ ሥራዋ ላይ ያልተገኘች በሙከራ ላይ የምትገኝ ዕጩ ዐቃቢተ ሕግ የወሊድ ፈቃዷ እንደተጠናቀቀ ቀሪውን የሙከራ ጊዜ እንድትጨርስ ይደረጋል፤

**11. Nullity of Employment and Appointment**

1/ An employment or appointment of any public prosecutor, based on false information given by him, shall be declared null and void at any time.

2/ A public prosecutor, whose appointment or employement declared null and void in accordance with Sub-article (1) of this Article, shall pay back the salary and other benefits he has received before the date of nullification measure.

**12. Probation**

1/ The probation period for a candidate public prosecutor shall be 6 (six) months. If a candidate public prosecutor's compiled performance evaluation result is below an average, the probation may be extended for additional 3 (three) months.

2/ If a candidate public prosecutor is unable to get an average or above compiled performance evaluation result for the extended probation period shall be terminated.

3/ Without prejudice to Article 22(5) and (6) of this Regulation, where the public prosecutor on probation is absent from his work due to employment injury, he shall be allowed to complete the remaining probation period following the date of his recovery.

4/ Where the public prosecutor on probation period isabsent due to force majeure for a period lessthan one month, the performance evaluationwill cover only the period in which he waspresent at work.

5/ Notwithstanding the provision of sub-Article (3) of this Article, a public prosecutor on probation is absent due to maternity leave, for a period of more than one month, she shall be allowed to complete the remaining probation period following the end of her maternity leave.

https://chilot.me



፮/ በዚህ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በሙከራ ላይ ያለ ዕጩ ዐቃቤ ሕግ ቋሚ ዐቃቤ ሕግ ያለው መብትና ግዴታ ይኖረዋል።

**፲፫. <u>የሙከራ ጊዜን ስለማጠናቀቅ</u>**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት ለሙከራ የተቀጠረ ዕጩ አቃቤ ሕግ በተወሰነለት የሙከራ ጊዜ መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የአፈጻጸም ውጤት ካስመዘገበ የትምህርት ደረጃውና የሥራ ልምዱ በሚመጥነው ደረጃ ለሙከራ ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በቅጥሩ መሰረት ይሾማል።

፪/ የዕጩ ዐቃቤ ሕጉ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ጊዜውን ጠብቆ ያልተሞላ እንደሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ (፩) እና (፪) የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈጻጸም ምዘና እንዲሞላ ተደርጎ ለሙከራ ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ በቅጥሩ መሰረት ይሾማል።።

**፲፬.<u>ስለ መታወቂያ</u>**

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ የጸደቀ መታወቂያ ይሰጠዋል።

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>የሥራ ሁኔታ</u>**

**<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>**

**<u>ስለ ዐቃብያነ ሕግ ነጻነት</u>**

**፲፭.<u>አቃብያነ ሕግ ነጻ ስለመሆናቸው</u>**

ዐቃብያነ ሕግ፡-

፩/ ከማናቸውም ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፤ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፤

፪/ በሕግና በተዘረጋ ሥርዐት መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከአቃቤ ሕግነት ሥራቸው አይነሱም።

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>በሥራ ላይ ስለመገኘት</u>**

**፲፮.<u>ስለመደበኛ የሥራ ሰዓት</u>**

፩/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ቀንና ሰዓት የአቃብያነ ሕግ የሥራ ቀንና ሰዓት ይሆናል፤

6/ Unless otherwise provided in this Regulation, during the probation period a candidate public prosecutor shall have, the same right and obligations that a permanent public prosecutor has.

**13. <u>Completion of Prohibitions Period</u>**

1/ where a candidate of public prosecutor on probation performance evaluation result is above an average as provided under Article 12 of this Regulation, he shall be appointed in a position he fits, having regard to his qualification and experience.

2/ if performance evaluation of a probationary public prosecutor is not carried out before the expiry date of the probation period and without prejudice to Article 12(1) and (2) of this Regulation, the performance evaluation shall be carried out within one month following the expiry date of the probation period and shall be appointed from the date of his recruitment as probationer.

**14. <u>Identity Card</u>**

Any public prosecutor shall receive identity card approved by the Office.

**<u>PART THREE</u>**

**<u>Condition of Work</u>**

**<u>Section one</u>**

**<u>Independence of Public Prosecutor</u>**

**15. <u>Independence of Public Prosecutor</u>**

Public prosecutors:

1/ shall perform their duty independently and being free in accordance with law without any other interference;

2/ shall not transfer from their duties except relevant law and established system;

**<u>Section Two</u>**

**<u>Attendance</u>**

**16.<u>Normal Hours of Work</u>**

1/ The working days and hours of government institutions shall be applicable to the working days and hours of public prosecutors.

https://chilot.me


፪/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ወደ ሥራው ዘግይቶ የሚመጣ ከሆነ፣ ቀደም ብሎ ከሥራው የሚወጣ ከሆነ ወይም በአንድ ምክንያት ከሥራው የሚቀር ከሆነ ይህንኑ ለቅርብ ኃላፊው ማሳወቅ አለበት፣

፫/ በመደበኛ የሥራ ሰዓት በሌላ ሥራ ወይም የሥራ ቦታ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ ይህንኑ ለቅርብ ኃላፊው መግለጽና ማስፈቀድ አለበት።

**፲፯.ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በላይ ስለመሥራት**

፩/ ሥራው የሚመለከተው የበላይ ሀላፊ ባዘዘ ጊዜ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከመደበኛው የሥራ ሰዓት በላይ መሥራት ግዴታው ነው፤

፪/ ዐቃቤ ሕጉ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት በላይ እንዲሠራ የሚታዘዘው ሊደረግለት የሚገባው ጥንቃቄና ድጋፍ ሁሉ ሳይጓደልበትና ሥራው በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሊፈፀም የማይችል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤

፫/ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፣ስለክፍያው መጠን እና የማካካሻ እረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

**፲፰.የሕዝብ በዓላት እና የሳምንት የዕረፍት ቀናት**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በሕዝብ በዓል፣ በሳምንት የዕረፍት ቀናት ወይም በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን ባለመሥራቱ መደበኛ የደመወዝ ክፍያ አይቀነስበትም፤

፪/ የሥራው ሁኔታ አስገድዶ በሕዝብ በዓል በሳምንት የዕረፍት ቀናት ወይም በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን እንዲሠራ የታዘዘ ዐቃቤ ሕግ ምርጫውን መሠረት በማድረግ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም የማካካሻ ዕረፍት ይሰጠዋል፣

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ የተደነገገው ቢኖርም የሥራው ሁኔታ አስገድዶ በሳምንት የዕረፍት ቀናት እንዲሠራ የታዘዘ ዐቃቤ ሕግ በተከታዩ ሳምንት ባለው የሥራ ቀን ውስጥ የማካካሻ ዕረፍት

2/ Any public prosecutor shall report his late arrival, early departure or other cases of absence to his immediate superior.

3/ A public prosecutor engaged in a different work or placeof work during normal hours of work shall reportand get permission same to his superior.

**17. Overtime**

1/ Any public prosecutor is obliged to work overtime when instructed by his superior;

2/ Overtime work shall be ordered with necessary care and support and only if the workcannot be done during normal working hours; and,

3/ the Office shall issue directive on theconditions of overtime work, amount ofpayment and compensatory leaveshall be determined by directives.

**18. Public Holidays and Weekly Rest Days**

1/ Any public prosecutor shall incur no reduction in his regular pay on account of having not worked on public holidays or weekly rest days or on any day offices are closed by the order of the government.

2/ Any public prosecutor ordered to work on a public holiday; a weekly rest day or on a day government institutions are closed by the order of the government, due to compelling circumstances, shall be entitled to overtime pay or compensatory leave based on his preference.

3/ Notwithstanding the provision of Article 17 of this Regulation a public prosecutor ordered to work on a weekly rest days, due to compelling circumstances, shall be granted a compensatory leave during working

እንዲሰጠው ይደረጋል።

days of the next week.

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለፈቃድ

### ፲፱.የዓመት እረፍት ፈቃድ

፩/ በማናቸውም የሥራ ደረጃ የተመደበ ዐቃቤ ሕግ ደመወዝ የሚከፈልበት የዓመት እረፍት ፈቃድ ያገኛል፤

፪/ ማንኛውም ዕጩ አቃቤ ሕግ የ ፲፩ (አሥራ አንድ) ወር አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የዓመት እረፍት ፈቃድ አይሰጠውም፤

፫/ ለአቃብያነ ሕግ የሚሠጣቸው የዓመት እረፍት ፈቃድ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

(ሀ) አንድ ዓመት ያገለገለ ዐቃቤ ሕግ ፳(ሃያ) የሥራ ቀን የዓመት እረፍት ፈቃድ ያገኛል፣

(ለ) ከአንድ አመት በላይ ያገለገለ ዐቃቤ ሕግ ላገለገለበት ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" በተመለከተው የፈቃድ ጊዜ ላይ አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ረፍት ፈቃድ ያገኛል። ሆኖም በዚህ አኳኋን የሚሰላው የዓመት እረፍት ፈቃድ ከ፴ (ሠላሳ) የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት የዐቃብያነ ሕግ የዓመት እረፍት ፈቃድ ሲሰላ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ በሌላ የሥራ መደብ ላይ ተመድቦ የሠራበት ጊዜ በዐቃቤ ሕግነት ተመድቦ ከሠራበት ጊዜ ጋር ተደምሮ ይታሰባል፤ ከሌላ የፌደራል ወይም የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት ልማት ድርጅት ተዛውሮ የመጣ ዐቃቤ ሕግ ወደ መሥሪያ ቤቱ ከመዛወሩ በፊት በሠራባቸው መሥሪያ ቤቶችና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ውስጥ ያበረከተው አገልግሎት ለዓመት እረፍት ፈቃዱ ስሌት ይታሰብለታል።

## Section Three

## Leave

### 19. Annual Leave

1/ A public prosecutor shall have the right to annual leave with pay.

2/ Any probationary public prosecutor shall not be entitled to annual leave before serving for 11 (eleven) months.

3/ The following annual leave shall be granted to public prosecutors;

a) twenty (20) working days for his first year of service;

b) a public prosecutor having a service of more than a year shall be entitled to additional leave of one working day for every additional year of service; provided, however, that the duration of annual leave shall not exceed thirty (30) working days.

4/ In calculating annual leave in accordance with sub-Article (3) of this Article, the length of services rendered by a public prosecutor in a different jobs with in the Office or in other federal or regional government institutions of public enterprise before transferring to the Office shall be counted.

https://chilot.me


**፳.የዓመት እረፍት ፈቃድ አሠጣጥ**

፩/ የዓመት እረፍት ፈቃድ ዘመን የሚባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጀት ዓመት ነው፤

፪/ የዓመት እረፍት ፈቃድ ሳይከፋፈል በአንድ ጊዜ በፈቃዱ ዘመን መወሰድ አለበት። ሆኖም በልዩ ልዩ ምክንያት የዓመት እረፍት ፈቃድ ተከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል፣

፫/ የዓመት እረፍት ፈቃድ የሚሠጠው በተቻለ መጠን የመሥሪያ ቤቱን ጥቅምና የዐቃቤ ሕጉን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጀው መርሐ ግብር መሠረት ነው፤

፬/ ዐቃቤ ሕጉ የዓመት እረፍት ፈቃዱን በሚወስድበት ጊዜ በእረፍት ላይ የሚቆይበትን ወር ደመወዙን በቅድሚያ ሊወስድ ይችላል፤

፭/ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ፈቃድ ወስዶ አግልግሎቱን በገዛ ፈቃዱ ያቋረጠ ዐቃቤ ሕግ አገልግሎት ያልሠጠበት ጊዜ ታስቦ በፈቃድ ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝ እንዲመልስ ይደረጋል።

**፳፩.የዓመት እረፍት ፈቃድን ስለማስተላለፍ**

፩/ አንድ ዐቃቤ ሕግ በሥራው አስፈላጊነት ምክንያት በፈቃዱ ዘመን የዓመት እረፍት ፈቃዱን ሙሉውን ወይም በከፊል ለመውሰድ ያልቻለ እንደሆነ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ወይም በሚመለከተው ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ፈቃዱ ወደ ሚቀጥለው የፈቃድ ዘመን ይተላለፍለታል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የዓመት እረፍት ፈቃድን ማስተላለፍ የሚቻለው ቢበዛ ለሁለት ተከታታይ የፈቃድ ዘመን ሆኖ ያልተጠቀመበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በሦስተኛው በጀት ዓመት ለዐቃቤ ሕጉ መሰጠት አለበት፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ሳይሆን በሌላ ምክንያት በሙሉ ወይም

**20. Granting of Annual Leave**

1/ The annual leave year shall be the fiscal year of the Government.

2/ Annual leave shall be taken without interruption at one time in the fiscal year. However, in special cases it may be permitted to take annual leave by installment.

3/ Annual leave shall be granted in accordance with aschedule designed with due regard to the interest ofthe public prosecutor and the Office.

4/ A public prosecutor shall be entitled to advance payment of his monthly salary at the time of taking his annual leave.

5/ A public prosecutor who resigns after taking his annual leave before the end of the budget year shall be liable to pay back part of theadvance salary for which he has not rendered service.

**21. Postponing Annual Leave**

1/ If the exigencies of the service unexpectedly prevents a public prosecutor from taking his full annual leave or part of it within the leave year, it shall be postponed by Attorney General or Deputy Attorney General to the next fiscal year.

2/ Any leave shall be postponed in accordance with sub-Article (1) of this Article, only for a maximum of two consecutive leave years and leave not taken shall be granted to the public prosecutor on third budget year.

3/ If for reasons other than those stated in sub Article (1) of this Article annual leave is not taken fully or partially it

https://chilot.me



በከፊል ያልተወሰደ የዓመት እረፍት ፈቃድ ቀሪ ይሆናል፤

shall be forfeited.

፬/ መሥሪያ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የዓመት እረፍት ፈቃድ ለሚተላለፍለትና ፈቃዱ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሠጠው ለሚጠይቅ ዐቃቤ ሕግ በጀት በቅድሚያ በማስያዝ ከተላለፈው የዓመት እረፍት ፈቃድ ውስጥ የመጀመሪያውን የአንዱን ዓመት የሥራ ቀናት ብቻ በማሰብ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሠጠው ማድረግ አለበት፤

4/ A public prosecutor, whose annual leave is postponed for two years in accordance with sub-Article (2) of this Article, may claim payment, and the Office shall make the payment for the number of working days for the first year of the accumulated annual leave from a budget allocated for such purpose.

፭/ የዐቃቤ ሕጉ አገልግሎት በመቋረጡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ተላልፎለት ያልወሰደው የዓመት እረፍት ፈቃድ የሥራ ቀናት ብቻ ታስቦ በገንዘብ ተለውጦ ይሠጠዋል።

5/ Where the appointment of a public prosecutor is terminated, the payment shall be made for the number of working days of unused annual leaves which are postponed.

## ፳፪. የሕመም ፈቃድ

፩/ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ የሙከራ ጊዜውን ከጨረሰ በኋላ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ሳይሆን በሌላ ሕመም ምክንያት ሥራ ለመሥራት ካልቻለ የሕመም ፈቃድ ያገኛል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሙከራ ጊዜውን ላጠናቀቀ ዐቃቤ ሕግ የሚሠጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው ፲፪ (አሥራ ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ከ፰ (ከስምንት) ወር ወይም በ ፬ ዓመት ውስጥ ከ፲፪ (አሥራ ሁለት) ወር አይበልጥም።

፫/ የሕመም ፈቃድ ከጥቅማጥቅም ጋር ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ይሠጣል፦

ሀ) ለመጀመሪያዎቹ ፮ (ስድስት) ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር፣

ለ) ለሚቀጥሉት ፪ (ሁለት) ወራት ለእያንዳንዱ ወር ከግማሽ የወር ደሞዝ ክፍያ ጋር፣

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪(፩) መሠረት በሙከራ ላይ ያለ ዕጩ አቃቤ ሕግ ከታመመ የሕክምና ማስረጃ የሚቀርብበት የ፩ (አንድ) ወር

## 22. Sick Leave

1/ If a public prosecutor at any level, having completed hi probation, is rendered incapable of work owing to sickness other than those resulting from occupational injury, he shall be entitled to sick leave.

2/ The leave referred to in sub-article (1) of this Article shall in no case be more than eight months counted consecutively or separately in the course of any twelve months period starting from the first day of his sickness. If a public prosecutor at any level has had twelve (12) months sick leave in the aggregate in a period of four (4) years, no further sick leave shall be granted.

3/ Sick leave including others benefits shall be granted in the following manner:

a) for the first six (6) months with full payment of his salary ;

b) for the next two (2) months with 50% payment of his salary;

4/ in accordance with Article 12(1) of this Regulation, a probationary public prosecutor shall be entitled to (1) one month sick leave with pay if confirmed by a medical

የሕመም ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ የተደነገገው ቢኖርም በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም አቃቤ ሕግ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስከሚመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የሕመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

፮/ ዐቃቤ ሕጉ ሕክምናውን በአግባቡ ባለመከታተሉ ወይም በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ሕክምናውን ያጓተተ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የሚሰጠው ሕክምና እና ፈቃድ ይቋረጥበታል።

፯/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በሕመም ምክንያት ከሥራ ሲቀር ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለመሥሪያ ቤቱ ማሳወቅ አለበት።

፰/ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ፡-

ሀ) በመታመሙ ምክንያት በተከታታይ ከ ፫ (ሦስት) ቀን ወይም በአመት ከ ፮ (ስድስት) ቀን በላይ ከሥራ ከቀረ መታመሙን የሚያረጋግጥ የሐኪም ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፤ የሐኪም ምስክር ወረቀቱ ከአቃቤ ሕጉ የግል ማሕደር ጋር ተያይዞ በምስጢር መጠበቅ አለበት።

ለ) ፈቃድ ላይ እያለ መታመሙን የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ካቀረበ የዓመት ፈቃዱ ተቋርጦ የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል።

## ፳፫. <u>የሕመም ፈቃድን ከዓመት የዕረፍት ፈቃድ ስለመቀነስ</u>

፩/ በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ የሐኪም ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በሕመም ከሥራ የቀረበት ቀን ተደምሮ ከ ፮ (ስድስት) ቀን በላይ ያለው ጊዜ ከዓመት

certificate.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-article (2) and (3) of this Article, any public prosecutor who has sustained an employment injury shall be entitled to injury leave with pay until he recovers and resumes work or until it is medically certified that he is permanently disabled.

6/ Where the public prosecutor intentionally delays his recovery by not following the treatment properly or by his non-observance of doctor's instructions, his entitlement of medical benefits and leave under Sub-article (2) and (3) of this Article shall cease.

7/ Where any public prosecutor absents himself from work on grounds of sickness he shall notify the Office the day following his absence, or unless it is impractical to notify.

8/ Public prosecutor found in any grade;

a) is absent from his work for more than three consecutive days or for more than six (6) days within a budget year due to sickness, he shall submit a medical certificate. The medical certificate shall be kept in his personal file confidentially;

b) submits sick leave medical certificate during his leave, the leave shall be terminated and granted the sick leave;

## 23. <u>Deduction of Sick Leavefrom Annual Leave</u>

1/ Where the aggregate number of days during which a public prosecutor is absent from Office, due to sickness without a medical certificate, exceeds six (6) days during the leave year, the number of days exceeding six (6) shall

https://chilot.me



የእረፍት ፈቃድ ላይ ይቀነስበታል።

፪/አቃቤ ሕጉ ከዓመት የእረፍት ፈቃድ የተረፈ ቀን የሌለው ከሆነ ከስድስት ቀን በላይ ያለው ቀን በተከታዩ የፈቃድ ዘመን ከሚታሰብለት የዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ላይ እንዲቀነስ ይደረጋል፤ ይህ ካልተቻለም ያለደመወዝ እንደተወሰደ ፈቃድ ይቆጠራል።

**፳፬.<u>የእርግዝናና የወሊድ ፈቃድ</u>**

፩/ ነፍሰ ጡር የሆነች ዐቃቢተ ሕግ፦

ሀ/ ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርምራ ለማድረግ መሥሪያ ቤቱ ከደሞዝ ጋር ፈቃድ ይሠጣታል፤ሆኖም አቃቢተ ሕግ ስለምርመራው የሐኪም ማስረጃ ማቅረብ አለባት።

ለ/ ከመውለዱ በፊት ሀኪም እንድታርፍ ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ታገኛለች።

፪/ ነፍሰጡር የሆነች አቃቢተ ሕግ መውለጃዋ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት የ፴ (ሠላሳ) ተከታታይ ቀን የቅድመ ወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ፺ (ዘጠና) ተከታታይ ቀን የወሊድ ፈቃድ ከደመወዝ ክፍያ ጋር ይሠጣታል።

፫/ አቃቢተ ሕጓ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ያልወሰደች ከሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የተሠጣት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከማለቁ በፊት ከወለደች ያልተጠቀመችበትን የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከወለደች በኋላ እንድትጠቀምበት ይደረጋል።

፬/ አቃቢተ ሕጓ የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት እረፍት በበጀት ዓመቱ ካላት የዓመት እረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የዓመት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት የዓመት እረፍት ፈቃድ ይተካል።

be deducted from his annual leave.

2/ In case no annual leave is left, the days shall be deducted from the next year's leave allowance, failing which the excess shall be considered as leave without pay.

**24. <u>Maternity Leave</u>**

1/ A pregnant public prosecutor shall be entitled to:

a) paid leave for medical examination in accordance with a doctor's recommendation; however, the pregnant public prosecutor shall present the medical certificate;

b) paid leave before delivery if recommended by adoctor.

2/ A pregnant public prosecutor shall be granted a period of 30 consecutive days of maternity leave with pay preceding the presumed date of her confinement and a period of 90 consecutive days of maternity leave after confinement.

3/ If the pregnant public prosecutor does not used prenatal leave or delivers on before the completion of prenatal leave which is granted under sub-article (2) of this Article, the unused prenatal leave will be granted after her confinement.

4/ If the pregnant public prosecutor does not deliver on the presumed date and the 30 days of her prenatal leave has elapsed, the days subsequently taken before the beginning of the prenatal period shall be counted outof the regular annual leave within the fiscal year or if not within the next fiscal year.

https://chilot.me



፭/ ማንኛዋም የስድስት ወር እስከ ስምንት ወር ነፍሰጡር የሆነች ዐቃቢተ ሕግ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከመውሰዱ በፊት ጽንሱ የተቋረጠባት ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ስታቀርብ የ፷(ሰልሳ) ቀን ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጣታል።

፮/ የጽንስ መቋረጥ ያጋጠማት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሳትወስድ ወይም ወስዳ ከሆነ የወሰደችው ፈቃዱ ተቋርጦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የ፺ (ዘጠና) ቀን ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጣታል።

፯/ ከሦስት እስከ ስድስት ወር ባለው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ የፅንስ መቋረጥ ያጋጠማት ዐቃቢተ ሕግ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ ስታቀርብ ደመወዝ የሚከፈልበት ፴ (ሠላሳ) ተከታታይ ቀን ፈቃድ ይሰጣታል።

፰/ የትዳር ጓደኛው የወለደች አቃቤ ሕግ ከወሊድ ጋር በተያያዘ ቤተሰቡንና ባለቤቱን ለመንከባከብ ደመወዝ የሚከፈልበት ፲ (አሥር) የሥራ ቀን ፈቃድ ይሠጠዋል።

**፳፭.የሐዘን ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፡-

ሀ) የትዳር አጋሩ ወይም

ለ) የራሱ ወይም የትዳር አጋሩ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህት ወይም ልጅ ቢሞት ደመወዝ የሚከፈልበት የ፭ (አምስት) ቀን የሀዘን ፈቃድ ይሠጠዋል።

፪/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ ከሞተበት በአንድ የፈቃድ ዘመን ውስጥ ከ ፮ (ስድስት) ቀን የማይበልጥ ደመወዝ የሚከፈልበት የአንድ ቀን የሀዘን ፈቃድ ይሠጠዋል።

**፳፮.ልዩ ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፡-

5/ Any pregnant public prosecutor if it isterminated the pregnancy within six months upto eight months before taking prenatal leave shall be granted 60 consecutive days of leave with pay when she is presented the medical certificate.

6/ When the termination of pregnancy occurs before taking prenatal leave or even if she used it shall be granted to 90 consecutive days of leave with pay in accordance with Sub-article (2) of this Article after terminating the leave taken.

7/ A pregnant public prosecutor shall be granted to 30 consecutive days of leave with pay, if the pregnancy is terminated with in three up to six months when she is presented the medical certificate.

8/ Any public prosecutor shall be entitled a paternity leave with pay for ten working days at the time of his wife's delivery.

**25. Mourning Leave**

1/ Any public prosecutor;

a) in cases of death of spouse;or,

b) his or his spouse father, mother,brother, sister, son or daughter, a public prosecutor shall be granted five (5) days mourning leave with pay.

2/ If a close relative or a close friend dies, a public prosecutor shall be granted a one day mourning leave with pay, not exceeding, however, six (6) days during a leave year.

**26. Special Leave**

1/ Any public prosecutor has the right to be granted special leave with pay in the following conditions.

https://chilot.me



ሀ) ጋብቻውን በሚፈጽምበት ጊዜ ፭ (አምስት) የሥራ ቀናት፣

ለ) ስለሚከታተለው ትምህርት ለሚወስደው ፈተና በማናቸውም ዓመት ፈተና ለሚወስድባቸው ቀናት በሙሉ፣

ሐ) የጥናቱ ፕሮፖዛል በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ታይቶ ሲፈቀድ ለሕግ ጥናትና ለምርምር ሥራ በአምስት ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ ለአራት ወር፣

መ) በማናቸውም ፍርድ ቤት፣ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ወይም ወደ ማናቸውም መርማሪ አካል እንዲቀርብ የሚያስገድደውን መጥሪያ ሲያቀርብ የተፈለገበትን ጉዳይ አከናውኖ ለመመለስ የሚያስፈልገው ጊዜ።

ሠ) አንድ ዓመት ያልሞላው ሕጻን ልጁን ለማሳከም በህክምና ማስረጃ ለተረጋገጠ ጊዜ፣

፪/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ፈቃድ የጠየቀበት ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ከሥራ ገበታው ተለይቶ በሀገር ውስጥ ወይም ከሀገር ውጪ በትምህርት ለማሳለፍ ሲሆን እና ትምህርቱን ተከታትሎ ሲያጠናቅቅ ለመሥሪያ ቤቱ የተሻለ አገልግሎት እንደሚያበረክት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ሲያምንበት የትምህርት ፈቃድ ሊሠጠው ይችላል። ፈቃድ የሚሠጥበት የጊዜ ርዝመትና ሌሎች ሁኔታዎች ዝርዝር በመመሪያ ይወሰናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚሠጠው የትምህርት ፈቃድ በየሁለት ዓመት ለሚደረግ የደመወዝ ጭማሪ ተፈላጊ ለሆነው የቆይታ ጊዜ አይታሰብለትም።

፬/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፫ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ አቃቤ ሕግ በበቂ ምክንያት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሠጠው ሲጠይቅ እና የመሥሪያ ቤቱን

a) for concluding marriage, five (5) working days;

b) for all examination days during the year for the course he has been enrolled;

c) to carry out legal research approved by theAttorney General, four (4) months once in every five (5)years;

d) when compelled to appear before any court, organ vested jurisdiction power by law or investigating organ, the necessary time for his appearance, on production of the summons.

e) for the timeconfirmed by medical certificate to follow up medical treatment of his child who has not attained the age of one year.

2/ Education leave may be granted to any public prosecutor where the leave is required for pursuing studies locally or abroad, provided the Attorney General is convinced that the public prosecutor's training contributes to render a service upon completion of his education; details of other conditions shall be determined by directive.

3/ Education leave granted under Sub-article 2 of this Article shall not be considered for a two-year salary increment.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1 to 3) of this Article, a public prosecutor who has completed his probation, upon sufficient ground, applies for a special leave without pay; the Attorney General may authorize the grant of such leave for not more than 1

https://chilot.me



ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ከአንድ አመት ለማይበልጥ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ ቢኖርም አቃቤ ሕጉ ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀው የመንግሥት መሥሪያ ቤትን በሚመለከት የፕሮጀክት ሥራ ላይ በመመደቡ ወይም በትዳር ጓደኛው ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሥራ በውጭ ሀገር መመደብ ምክንያት ከሆነ ልዩ ፈቃዱ የፕሮጀክት ወይም የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ሥራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ላለው ጊዜ ይሆናል፡፡

**፳፯.** **ያለፈቃድ ከሥራ ስለመቅረት**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሳይፈቀድለት በማናቸውም ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ለቀረበት ጊዜ ደመወዝ አይከፈለውም፡፡

፪/ አቃቤ ሕጉ ከሥራ ለቀረበት ጊዜ በቂ ምክንያት ያቀረበ እንደሆነ ከሥራ የቀረበትን ጊዜ ሙሉ ደመወዝ ያገኛል፡፡

**፳፰.** **ስለ ፈቃድ አጠያየቅ**

በጽሑፍ ለመጠየቅ የማይቻልበት ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚጠይቀው ፈቃድ ሁሉ በጽሑፍ መሆን አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት
## ስለዝውውርና ድልድል

**፳፱.** **መርህ**

አንድ ዐቃቤ ሕግ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም ከአንድ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ ተዛውሮ እንዲሠራ የሚደረገው መሥሪያ ቤቱ በሚያደርገው ዝውውር መሠረት ወይም የሚመለከተው አቃቤ ሕግ በሚያቀርበው የዝውውር ጥያቄ መሰረት ይሆናል፡፡

**፴.** **በመሥሪያ ቤቱ ስለሚደረግ የዐቃብያነ ሕግ ዝውውር**

፩/ መሥሪያ ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ ሲሆንና ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈፀም ሲባል የሥራውን

(one) year if it does not adversely affect the interest of the Office.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-article(4) of this Article a public prosecutor may grant special leave without pay if the request is related with projects of government office assignmentor spouse assignment in foreign diplomatic mission until the end of the project or diplomatic mission.

**27.** **Unauthorized Absence**

1/ Where a public prosecutor is absent from duty without permission, the necessary arrangements for withholding his salary for the days of his absence shall be made.

2/ If the public prosecutor produces sufficient reasons for his absence, he shall get full payment for the time of absence.

**28.** **Application for Leave**

All leave shall be requested in writing unless the public prosecutor is encountered with situations preventing him to do so.

## Section Four
## Transfer and Redeployment

**29.** **Principle**

A public prosecutor may be transferred from place to place or from one job to another by the Office or upon the requests of the prosecutor for such transfer.

**30.** **Transfer of Prosecutor by the Office**

1/ The Office may transfer a public prosecutor from one place to another or from one job to another when

https://chilot.me


ማነስና መብዛት፣ የአቃቤ ሕጉን ትጋትና የሥራ ውጤታማነት፣ የቆይታ ጊዜውን በማመዛዘን ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የደረጃ መብትና ጥቅሙን ሳያጓድል ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ወይም ከአንድ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ ሊያዛውረው ይችላል።

፪/ አቃቤ ሕጉ ከሚሠራበት ክልል ወደ ሌላ ክልል በመሥሪያ ቤቱ ከተዛወረ ለራሱና ለቤተሰቡ የጉዞና የጓዝ ማጓኘ ወጪ በአንድ ወር ውስጥ ይከፈለዋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በመሥሪያ ቤቱ በየጊዜው የሚፈፀም የአቃብያነ ሕግ ዝውውር በዋና ጉባኤው ተጠንቶና በተቻለ መጠን በዕቅድ ተይዞ መከናወን ይኖርበታል።

**፴፩.<u>በዐቃቤ ሕግ ወይም ከመስሪያ ቤቱ ውጪ ያለ ባለሙያ ስለሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ</u>**

፩/ በማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ:-

ሀ) በፁሁፍ ሆኖ በአቃቢያነ ህግ አስተዳደር ፅህፈት ቤት አማካኝነት ለዋናው ጉባኤ ይቀርባል።

ለ) ዋና ጉባኤው የቀረበውን የዝውውር ጥያቄ መርምሮ አስተያየቱን ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ያቀርባል፤ዋና ጉባኤው አስተያየቱን ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ከማቅረቡ በፊት ዝውውር የጠየቀውን ዐቃቤ ህግ የቅርብ ኃላፊ አስተያየት መጠየቅ ይችላል፣ጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

ሐ) በጤና ችግር ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ካልተፈቀደ በቀር አንድ ዐቃቤ ህግ የዝውውር ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት በተመደደበበት ቦታ ቢያንስ ሁለት አመት ማገልገል አለበት።

፪/ ከመስሪያ ቤቱ ውጪ ያለ ባለሞያ፡-

ሀ) ወደ መስሪያ ቤቱ ለመዛወር ጥያቄውን ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ማቅረብ ይችላል።

necessary and for the expeditious execution of the work, taking into account the work load and diligence duration of the public prosecutor provided that the public prosecutor's benefits are not negatively affected.

2/ When a public prosecutor transfers from one region he is working to another region by the Office,he shall be paid transportation and expense fee for himself, his family and properties within one month.

3/ Transfer of public prosecutors by the Office referred to in sub article (1) of this Article shall be carried out on the basis of a study by the Higher Commission and as much as possible according to plan.

**31. <u>Application of Transfer from Prosecutors or other Professionals Outside the Office</u>**

1/ Application for transfer by any public prosecutor shall be made:

a) In writing to the Higher Commission upon recommendation by the public prosecutor Administration Commission Office.

b) The Higher Commission shall examine the application for transfer and submit its opinion to the Attorney General.The Higher Commission may seek the opinion of the immediate head of the public prosecutor requesting the transfer before giving its opinion to the Attorney General.The decision of the Attorney General shall be final.

c) unless authorized by the Attorney General on the ground of health problem or for any other convincing reason,a public prosecutor shall serve at least for two years in the place where he has been assigned before applying for transfer.

2/ Other Professional outside the Office:

a) may submit his transfer application to the Attorney General.

https://chilot.me


ለ) ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ የቀረበለትን የዝውውር ጥያቄ አስመልክቶ በዐቃቤ ህጉ አስተዳደር ጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብለት ያደርጋል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ መሰረት የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ በፌደራል የመንግስት ሰራተኞች ህግ መሰረት ይመራል፡፡

፫/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ "ሀ" እና "ለ" የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጪ ዝውውር ዝርዝር አፈፃፀምን በተመለከተ ተቋሙ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

**፴፪.ስለድልድል**

፩/ መሥሪያ ቤቱ አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ዐቃብያነ ሕግን በማወዳደር ደልድሎ ማሠራት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚደለደል ዐቃቤ ሕግ ቀደም ሲል ይዞት በነበረው ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ የነበረው ደመወዙና ጥቅማጥቅሞቹ አይቀነሱበትም፡፡

**ንዑስ ክፍል አምስት**

**ስለ ደመወዝ**

**፴፫.የደመወዝ መደብ**

መሥሪያ ቤቱ በልዩ ልዩ ደረጃ ለሚቀጠሩ፣ ለሚመደቡ ወይም ለሚሾሙ ዐቃብያነ ሕግ የዐቃቤያነ ሕግን የሥራ ሁኔታና የመንግሥትን የፋይናንስ አቅም ያገናዘበ ተነጻጻሪ ነጻነታቸውን ማስጠበቅ የሚያስችል፣ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን መሳብና ማቆየት የሚያስችል የደመወዝ ስኬል ያወጣል፡፡

**፴፬.የመነሻ ደመወዝ**

አዲስ የሚመደብ ዐቃቤ ሕግ ለተመደበበት የሥራ ደረጃ የተወሰነው የመነሻ ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡

**፴፭.ሹመት ሲሠጥ ስለሚፈቀድ የመነሻ ደመወዝ**

፩/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ሹመት ሲሠጠው ከመሾሙ

b) the Attorney General shall order to the public Prosecutor Administration Council to submit recommendation.

c) the application of transfer provided under this sub article shall be governed by the Federal Civil Servant Law.

3/ Notwithstanding to article 2 (a) and (b) of this article ,the institution shall enact a directive about the implemntaion of external transfer.

**32. Redeployment**

1/ The Office shall redeploy public prosecutors on the basis of competition when it implements a new organizational structure.

2/ A public prosecutor redeployed pursuant to Sub Article (1) of this Article shall be entitled to his previous salary and benefits acquired by virtue of his grade and service.

**Section Five**

**Salary**

**33. Salary Scale**

Salaries payable to public prosecutor employed, assigned or appointed atdifferent grades shall be enable to administer themselves and their families in accordance with working conditions of public prosecutors and capacity of government finance.

**34. Starting Rate**

A newly assigned public prosecutor shall be paid the starting rate of the grade he is assigned to.

**35. Starting Rate for Appointment**

1/ Where a public prosecutor is appointed, he shall receive

https://chilot.me



በፊት ሲያገኝ የነበረው ደመወዝ ለተሾመበት ደረጃ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በታች ከሆነ ለደረጃው የተወሰነውን የመነሻ ደመወዝ ያገኛል።

፪/ ከመሾሙ በፊት ሲያገኝ የነበረው ደመወዝ ለተሾመበት ደረጃ ከተወሰነው የመነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ አዲስ ደመወዙ ከመሾሙ በፊት ያገኝ ከነበረው ደመወዝ ቀጥሎ ባለው የእርከን ደመወዝ ላይ ይሆናል።

## ፴፮.በደረጃ ተመሳሳይ ወደ ሆነ ሥራ ስለመዛወር

፩/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ከያዘው ሥራ ተመሳሳይ ወደሆነ ሌላ ሥራ ሲዛወር ወይም ሲመደብ ደመወዙና ደረጃው ቀድሞ የነበረው ይሆናል።

፪/ ዐቃቤ ሕጉ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ ደረጃ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ላይ ሊሠራ አለመቻሉ በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ሀ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብበት የሚችል ክፍት የሥራ ደረጃ ካለ በያዘው ደረጃ፣ ወይም

ለ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ደረጃ ከሌለና ዐቃቤ ሕጉ ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ፣

ወደሚስማማው የሥራ ደረጃ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል።

፫/ በመሥሪያ ቤቱ የሚደረግ ዝውውር በዋና ጉባኤው ተጠንቶና በተቻለ መጠን በእቅድ ተይዞ ግልጽ አሠራርን የተከተለ መሆን አለበት።

## ፴፯.ከፍ ወደአለ የሥራ ደረጃ በተጠባባቂነት ስለመመደብ

፩/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ከፍ ወደ አለ የሥራ ደረጃ በተጠባባቂነት ሲመደብ ደመወዙ ቀድሞ ሲያገኝ ከነበረው አይለወጥም።

፪/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ከፍ ወደአለ የሥራ ደረጃ በተጠባባቂነት ተመድቦ መቆየት የሚችለው ለአንድ አመት ብቻ ነው።

a starting salary of the grade he has been appointed to if the salary he was receiving before his appointment is less than the starting salary of the new grade.

2/ Where the salary he was receiving before his appointment is more than or equal to the starting salary of the new grade his new salary shall be theone specified at the next higher step.

## 36. Transfer to Work of Equal Position

1/ Where a public prosecutor is transferred or is assigned to another work of a similar nature, his salary and position shall remain the same.

2/ Where a public prosecutor is certified in medical certificate unable to work in his assigned position and place shall assign or transfer:

a) to another work of a similar nature if there is open work grade;

b) to another work of lower grade if there is no open work grade and the public prosecutor agreed to work in lower grade;

3/ Transfer in the Office shall be made on the basis of study by the Higher Commission with plan and transparent procedure as possible.

## 37. Acting Assignment to a Higher Position

1/ The salary of a public prosecutor assigned in a higher acting capacity shall remain the same.

2/ A public prosecutor may be assigned in a higher acting capacity for one year only.

https://chilot.me



፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ አመት በላይ ለሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና የሄደን ዐቃቤ ሕግ የትምህርቱ ወይም የስልጠናው ጊዜ እስኪጠናቀቅ ድረስ በሥራ ደረጃው ላይ በተጠባባቂነት ሌላ ዐቃቤ ሕግ መድቦ ማሠራት ይቻላል።

፬/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከፍ ወደአለ የሥራ ደረጃ በተጠባባቂነት ሲመደብ የተጠባባቂነት አበል ይከፈለዋል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

**፴፰.** **<u>ከደረጃ ዝቅ ስለማድረግ</u>**

አንድ ዐቃቤ ሕግ በዲሲፕሊን ጥፋት ወይም የሥራ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ ከደረጃው ዝቅ እንዲል ዋና ጉባኤው ሲወስን ደመወዙ እንደነገሩ ሁኔታ ዐቃቤ ሕጉ ዝቅ ባለበት ደረጃ መነሻ ደወመዝ ወይም ከመነሻው ደመወዝ ቀጥሎ ባለ በማናቸውም የእርከን ደመወዝ ላይ ሊመደብ ይችላል።

**፴፱.** **<u>በየጊዜው ስለሚደረግ የደመወዝ እርከን ጭማሪና ማበረታቻ</u>**

፩/ በዚህ ደንብ ውስጥ በሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ዐቃቤ ሕግ ለያዘው ደረጃ በደመወዝ ስኬል ውስጥ የተመለከተውን የእርከን ጭማሪ በየሁለት ዓመት የሚያገኘው:-

ሀ) በሥነ-ምግባሩ የተመሰገነና በሥራ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ሆኖ ሲገኝ፣ እና

ለ) ደመወዙ ለደረጃው ከተወሰነው ጣሪያ ያላለፈ እንደሆነ

ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚደረገው የደመወዝ ጭማሪ መጠን የጭማሪ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት ዐቃቤ ሕጉ ሲያገኝ በነበረው ደመወዝና ቀጥሎ በሚገኘው የደመወዝ እርከን መካከል ያለው ልዩነት ይሆናል።

፫/ የሥራ አፈጻጸም ውጤትን መሠረት በማድረግ ለዐቃብያነ ሕግ ማበረታቻ ይሰጣል።ዝርዝር አፈጻጸሙ በመመሪያ ይወሰናል።

3/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (2) of this Article a public prosecutor may be assigned to work grade in acting capacityto replace a public prosecutor who is on education or training program, that lasts more than one year.

4/ Any public prosecutor assigned in higher acting capacity shall be entitled to acting allowance; details shall be determined by a directive.

**38.** **<u>Demotion</u>**

Where a public prosecutor is demoted by the Higher Commission for disciplinary offence or inefficiency, his salary may, as the case may be, the starting rate or any salary next to the starting rate of position he is demoted to.

**39.** **<u>Periodic Salary Increments and Motivation</u>**

1/ Without prejudice to other provisions of this Regulation a public prosecutor shall be entitled to periodic increment of salary referred to in the salary scale every two years where:

a) his conduct is reputable and his performance has been satisfactory; and,

b) his salary does not exceed the maximum salary of his grade.

2/ The increment referred to in sub article (1) of this Article is the difference in amount between the salary that the public prosecutor has been receiving before a decision to give increment and the next step.

3/ Motivation shall be provided for a public prosecutor based on the performance evaluation result; details shall be determined by a directive.

https://chilot.me


**፵.እርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ አቆጣጠር**

በዚህ ደንብ መሠረት በየሁለት ዓመት የሚሠጥ የደመወዝ እርከን ጭማሪ የመቆያ ጊዜ የሚቆጠረው ዐቃቤ ሕጉ ከተሾመበት ወይም የመጨረሻውን ጭማሪ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**፵፩.ሹመት በእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ ላይ ስለሚኖረው ውጤት**

አንድ ዐቃቤ ሕግ በሹመት ምክንያት የሚያገኘው ደመወዝ ባይሾም ኖሮ በሚቀጥለው የጭማሪ ጊዜ ማግኘት ከሚችለው የደመወዝ እርከን እኩል የሆነ እንደሆነ፣የሚቀጥለው የእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜው ከሹመቱ በፊት ጭማሪ ካገኘበት ቀን ጀምሮ ይቆጠራል፡፡

**፵፪.ከደረጃ ዝቅ ማለት በእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜ ላይ ስለሚኖረው ውጤት**

በዲሲፕሊን ጥፋት ወይም የሥራ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ባለመሆኑ አንድ ዐቃቤ ሕግ ቀደም ሲል ከያዘው ደረጃ ዝቅ የተደረገ እንደሆነ የእርከን ጭማሪ መቆያ ጊዜው በደረጃ ዝቅ ካለበት ቀን ጀምሮ ይቆጠራል፡፡

**፵፫.የደመወዝ ጭማሪ አፈጻጸም**

መሥሪያ ቤቱ ለዐቃብያነ ሕግ የሚጠየቀውን የደመወዝ ጭማሪ ከዓመት በጀቱ ጋር ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

**፵፬.ስለ ደመወዝ ክፍያ**

፩/ የዐቃብያነ ሕግ ደመወዝ የሚከፈለው በየወሩ ከሃያ ስድስተኛው (፳፮) ቀን አንስቶ እስከ ወሩ የመጨረሻ ቀን ይሆናል፡፡

፪/ የማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ደመወዝ:-

ሀ) ዐቃቤ ሕጉ ስምምነቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣

ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም

ሐ) በሕግ በተደነገገው መሠረት፣

ካልሆነ በቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፡፡

**40. Calculation of Increment Waiting Period**

The two year waiting period for salary increment inaccordance with this Regulation shall commencerunning from the date of appointment of the public prosecutoror last increment he was granted.

**41. Effects of Appointment on Increment Waiting Period**

Where the salary of a public prosecutor as a result of his appointment to a higher grade is equal to that of the next step salary for which he would have been eligible had he not been appointed, the waiting period for the next periodic increment shall continue to run from the date of the last periodic increment in the grade from which he was appointed to.

**42. Effects of Demotion on Increment Waiting Periods**

Where a public prosecutor is demoted for reasons of disciplinary breach or inefficiency, the waiting period shall begin to run as of the effective date of such demotion.

**43. Execution of Salary Increment**

The Office shall submit to the Ministry of Finance its request for periodic increment for public prosecutors together with its fiscal year.

**44. Payment of Salary**

1/ The salary of public prosecutors shall be paid starting from every 26th day of each month as of the Ethiopian Calender to the final day of the month.

2/ The salary of any public prosecutor shall not be attached or deducted except in accordance with:

a) a written consent of the civil servant;

b) court order; or

c) the provisions of the law.

https://chilot.me


፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ወይም (ሐ) መሠረት ከዐቃቤ ሕጉ በየወሩ የሚቆረጠው ደመወዝ ተጣርቶ ከሚደርሰው አንድ ሦስተኛ አይበልጥም።

**፵፭.ስለልዩ ልዩ አበሎች**

ለማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የሚከፈል ማናቸውም ዓይነት አበል በዋና ጉባኤው ተጠንቶ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት
## ስለ ሕክምናና የጉዳት ካሳ

**፵፮.በሥራ ላይ የደረሰ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት በመጣ ሕመም ስለሚከፈል የጉዳት ካሣ**

፩/ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት በመጣ ሕመም ዘላቂና ሙሉ የአካል ጉዳት ደርሶበት ሥራ መሥራት የማይችል ዐቃቤ ሕግ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት መብትና ጥቅሙ ይከበርለታል።

፪/ አንድ ዐቃቤ ሕግ በሥራ ላይ በደረሰ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት በመጣ ሕመም ዘላቂ የሆነ ከፊል የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነና የደረሰውም ጉዳት ሥራውን ሙሉ በሙሉ እንዲያቋርጥ የማያስገድደው ሲሆን ሥራውን የሚቀጥል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰበት የአካል ጉዳት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት መብትና ጥቅሙ ይከበርለታል።

፫/ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ከባድ የመልክ መበላሸትን ያስከተለ ጉዳት የመሥራት ችሎታ ማጣትን ባያስከትልም ለጉዳት ካሳ አከፋፈልና ለሌሎች ጥቅማጥቅሞች አሠጣጥ ሲባል እንደዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ይቆጠራል።

**፵፯.ሕክምና አገልግሎት ስለማግኘት**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሲታመም የሕክምና ወጪው ሙሉ በሙሉ በመሥሪያ ቤቱ እየተሸፈነለት በተመላላሽም ሆነ በሆስፒታል ተኝቶ የመታከም መብት አለው።

3/ Monthly deductions from the salary of a public prosecutor to be made pursuant to Sub-article (2) (b) or (c) of this Article shall not exceed one third of his net salary.

**45. Allowances**

The higher commission shall undertake studies about any allowance payable to any public prosecutor and shall be determined by a directive to be issued.

## Section Six
## Medical Benefits and Damages

**46. Damages in Case of Employment Injuries or Occupational Disease**

1/ The right of a public prosecutor permanently and totally disabled due to employment injury or occupational disease shall be entitled to benefits provided with the relevant pension law.

2/ Where a public prosecutor has suffered permanent and partial disablement caused by employment injury or occupational disease, but is still fit for work, he shall continue in his work. He shall, however, be entitled to compensation and benefits provided with the relevant pension law.

3/ Injuries which, although not resulting in incapacity for work, cause series mutilation or disfigurement of the injured public prosecutor, shall be considered permanent partial disablement, for the purpose of payment of compensation and other benefits.

**47. Medical Benefits**

1/ A public prosecutor shall have the right during his sickness, to be treated in a hospital as an in-patient or out-patient and the full medical expenses shall be covered by the Office.

፪/ የዐቃቤ ሕግ የትዳር አጋር ወይም ሃያ አንድ አመት ያልሞላው ልጅ ሲታመም ግማሽ የሕክምና ወጪ በመሥሪያ ቤቱ እየተሸፈነለት በተመላላሽም ሆነ ሆስፒታል ተኝቶ የመታከም መብት አለው፡፡

፫/ መሥሪያ ቤቱ ዐቃብያነ ሕግ ሊታከሙ የሚችሉባቸውን መንግስታዊ የሕክምና ተቋማት ሊመርጥ ወይም ሊወስን ይችላል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሰባት**

**ስለዐቃብያነ ሕግ የሚቀርብ ዘገባ**

**፵፰.ስለዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈፃፀም ዘገባ**

፩/ እያንዳንዱ የቅርብ ሃላፊ የሚቆጣጠራቸውን ዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈፃፀም በአግባቡ በመከታተልና በመገምገም በየዓመቱ ታኅሳስ ፴ እና ሰኔ ፴ ቀን ዘገባ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ዘገባው የሚቀርብለት የበላይ ዐቃቤ ሕግም በዘገባው ላይ እንዲፈርምበት ያስፈልጋል፡፡

፪/ ግልጽ ዓላማ፣ ወጥ መሥፈርት እና ተነጻጻሪ ደረጃ የያዘ የዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈፃፀም መለኪያ በዋና ጉባኤው ተጠንቶ በመሥሪያ ቤቱ ይፀድቃል፡፡

**፵፱.በሙከራ ላይ ስላለ ዐቃቤ ሕግ የሚቀርብ ዘገባ**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ በተመለከተው መሠረት በሙከራ ላይ ስላለ ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃፀም የሚዘጋጅ የመጀመሪያ ዘገባ ዐቃቤ ሕጉ ከተቀጠረበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ የ ፫(ሦስት) ወር ጊዜ እንዳለቀ መቅረብ አለበት፤ ሁለተኛው ዘገባ ደግሞ የሙከራ ጊዜው ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፡፡

፪/ የሙከራ ጊዜው የተራዘመ እንደሆነ የተራዘመው ጊዜ ከማለቁ ፲፭ (አሥራ አምስት) ቀን አስቀድሞ ለሙከራ ስለተቀጠረው ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃጸም ዘገባ መቅረብ አለበት፡፡

2/ Where the spouse or the child who has not attained the age of twenty one (21) years are sick shall have the right, during their sickness,to be treated in a hospital as an in-patient or out-patient and half of the medical expense shall be covered by the Office.

3/ The Office may select or designate government medical institutions where public prosecutors may be treated.

**Section Seven**

**Reports Concerning Public Prosecutors**

**48. PublicProsecutors Efficiency Reports**

1/ Every immediate head of public prosecutor shall supervise and evaluate the performance of public prosecutors under his supervision and submit efficiency report every year by the end of the months of Tahisas and Sene. The superior public prosecutor who receives the report shall counter sign it.

2/ The Higher Commission shall undertake studies for clear objectives, uniform criteria and complimentary grades of performance evaluation and approved by the Office.

**49. Efficiency Report During Probation**

1/ The first efficiency report about a public prosecutor on probation referred to in Article 12 of this Regulation shall be submitted three (3) months after his employment. The next report shall be made one month before the completion of the probation period.

2/ where the probation period is extended, efficiency report shall be submitted fifteen days before the expiry of the extended period of probation.

https://chilot.me


## ፶.ስለሥራ አፈፃፀም ዘገባዎች አያያዝ

፩/ ስለ ዐቃብያነ ሕግ የሥራ አፈፃፀም የሚቀርቡ ዘገባዎች ሁሉ በዐቃቤ ሕጉ የግል ማሕደር ውስጥ ተያይዘው መቀመጥ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ የዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃፀም ዘገባ በምሥጢር መጠበቅ አለበት፡፡

## ፶፩. ስለ ሥራ አፈፃፀም ጉድለት የሚቀርቡ ዘገባዎች

፩/ ስለአንድ ዐቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃፀም በቀረበው ዘገባ ዐቃቤ ሕጉ ያገኘው አማካይ ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ዘገባ አቅራቢው የቅርብ ሃላፊ ስለዘገባው ከሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ ጋር መነጋገር አለበት፤ የሥራ አፈፃፀም ዘገባ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግም ስለዘገባው ያለውን አስተያየት በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ ዐቃቤ ሕጉ የሚሠጠው አስተያየት ከዘገባው ጋር በግል ማሕደሩ ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

፪/ በተሞላው የሥራ አፈጻጸም ውጤት ላይ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ ቅሬታ ያለው ከሆነ ቅሬታውን በ ፲፭ (አሥራ አምስት) ቀን ውስጥ ለቅርብ ሃላፊው የበላይ ሃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የቀረበው ቅሬታ የሥራ አፈጻጸሙን በሞላው የቅርብ ሀላፊና በእርሱ የበላይ ሃላፊ በጋራ ታይቶ በበላይ ሃላፊው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬/ በበላይ ሃላፊው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ዐቃቤ ሕግ በ፲ ቀን ውስጥ ቅሬታውን ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ማቅረብ ይችላል፡፡የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 50. Maintenance of Efficiency Reports

1/ All efficiency reports shall be kept in the personal file of the public prosecutor concerned.

2/ Efficiency reports of a public prosecutor submitted at anytime under this Regulation shall be kept confidentially.

## 51. Inefficiency Reports

1/ Where the efficiency report of a public prosecutor is below average, the reporting public prosecutor or official shall discuss the report with the concerned public prosecutor.The public prosecutor about whom the report has been submitted may give remarks in writing on the report and the remarks shall be filed in the personal file together with the report concerned.

2/ Where a public prosecutor has objections on the efficiency report, he shall report his objection to the superior of his immediate official with in 15 (fifteen) days.

3/ Objections reported in accordance with Sub-article (2) of this Article, the reporting official and his superior shall see the case together. The decision of the superior shall be final.

4/ a public prosecutor aggrieved by the decision of the superior, may appeal to the Attorney General within 10 (ten) days. The decision of the Attorney General shall be final.

https://chilot.me



**፶፪.ስለችሎታ ማነስ የሚቀርብ ዘገባ**

ማንኛውም በቋሚነት የተቀጠረ ዐቃቤ ሕግ ችሎታው እጅግ ዝቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ከሥራ የመሰናበት ውሳኔ የሚሠጥበት ሁኔታ ሲኖር ዘገባ አቅራቢው በዘገባው ላይ "የችሎታ ማነስ" የሚል ምልክት ያደርግበታል፡፡

**ንዑስ ክፍል ስምንት**

**ስለ አቤቱታ**

**፶፫.መርህ**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከሥራው ጋር በተያያዘ ስለደረሰበት በደል አቤቱታ ለማቅረብ መብት አለው፤ ሆኖም አቤቱታውን ለማቅረብ የሚችለው በደሉ ተፈፀመብኝ ከሚልበት ጊዜ ጀምሮ ቢያንስ ፳፬ ሰዓት ካለፈ በኋላ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቀርበው አቤቱታ በጽሑፍ ሆኖ ለአቤት ባዩ ዐቃቤ ሕግ የቅርብ ኃላፊ መቅረብ አለበት፡፡ አቤቱታው በ ፮ (ስድስት) ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**፶፬.አቤቱታን ስለማጣራትና ውሳኔ ስለመስጠት**

፩/ አቤቱታ የቀረበለት የቅርብ ሀላፊ አቤቱታው ከቀረበለት ቀን አንስቶ በ ፲ (በአሥር) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፪/ አቤቱታ የቀረበለት የቅርብ ሀላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢ ውሳኔ ያልሠጠበት እንደሆነ ወይም አቤት ባዩ ዐቃቤ ሕግ በውሳኔው ያልተስማማበት ከሆነ ጉዳዩን ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ለማቅረብና ለማሰማት ይችላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ስለአቤቱታው ተገቢው ምርመራ እንዲደረግ ማዘዝ ይችላል፡፡

**52. Adverse Reports**

In case where the efficiency of a permanently employed prosecutor is extremely low to warrant his dismissal, the reporting official shall mark on the report “adverse report”.

**Section Eight**

**Complaint**

**53. Principle**

1/ Any public prosecutor shall have the right to apply grievances related with his duties; however, such complaint shall be made after at least twenty-four (24) hours from the incident occurred.

2/ a complaint lodged in accordance with sub-article (1) of this Article shall be made in writing to the immediate head of the public prosecutor who lodges the complaint. If the complaint is not lodged with in six (6) months shall be revoked in limitation period.

**54. Investigation and Decision on the Complaint**

1/ The immediate head shall give appropriate decision with in ten (10) consecutive working days up on receiving the complaint.

2/ If the immediate head does not give appropriate decision on the complaint within the time limit referred to in Sub-article (1) of this Article, or if the complainant disagrees over the decision, he has the right to submit the complaint to the Attorney General.Where necessary, the Attorney General may order appropriate investigation of the complaint.

https://chilot.me


## ንዑስ ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ሥልጠና

### ፶፭.ስለ ሥልጠና መርሐ ግብር

መሥሪያ ቤቱ ሀላፊነቱን በብቃት ለመወጣት እና የሚቀይሳቸውን አላማዎች ማሳካት እንዲችል፡-

፩/ በቅጥር ወይም በዝውውር አፈጻጸም ሥነሥርዓት አዲስ ለሚቀጠሩ ወይም ለሚመደቡ ዐቃቢያነ ሕግ ስለመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት፣ፖሊሲዎችና የአፈፃፀም ሥርዓቶች፣ የአሠራር ልምዶች፣ ደንቦች እንዲሁም ስለሚመደቡበት ሥራ አጠቃላይ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ የመሥሪያ ቤቱን እና የሥራ አካባቢያቸውን እንዲያውቁና እንዲላመዱ የሚያግዝ የመተዋወቂያ መርሐ ግብር ያዘጋጃል።

፪/ ዐቃብያነ ሕግ በተመደቡበት ሥራ ውጤታማና ቀልጣፋ ይሆኑ ዘንድ በየጊዜው የሚፈጠሩ አዳዲስ የሞያ እውቀቶችን እንዲሁም የአሠራርና የግንኙነት ዘዴዎችን በመቅሰምና የልምድ ልውውጥ በማድረግ የሞያ እውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ፣የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉና በተጨማሪም በሀላፊነት ደረጃ የተመደቡት የአመራር ብቃታቸውን ለማጎልበት እንዲችሉ በመሥሪያ ቤቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የስልጠና መርሐ ግብር ያቅዳል፣ያስፈጽማል።

### ፶፮.ስለ ስልጠና መርሐ ግብር አፈፃፀም

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚዘጋጀው የመተዋወቂያ መርሐ ግብር በመሥሪያ ቤቱ ይከናወናል።

፪/ መሥሪያ ቤቱ አቃብያነ ሕግን ለማሠልጠን የሚያዘጋጀው የሰው ኃይል ሥልጠና መርሐ ግብር እንደሁኔታው በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚገኙ አግባብ ባላቸው ተቋሞች ሙሉ በሙሉ ወይም በትብብር ሊከናወን ይችላል።

### ፶፯.ስለ ሠልጣኝ አቃብያነ ሕግ ግዴታ

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ፡-

፩/ መሥሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው አግባብ ባለው የስልጠና መርሐ ግብር በሙሉ ፈቃደኝነት የመሳተፍ፣

## Section Nine

## Training

### 55. Training Schemes

To accomplish its responsibilities efficiently and achieve its objectives, the Office shall:

1/ prepare orientation schemes for new entrants with employment or transfer to familiarize them with the working environment, the structure, policies, the nature of the work and working procedure of the Office;

2/ design and execute training schemes that enhance efficiency through training on new idea and practice and through exchange of experience, thus increasing their professional knowledge and horizon as well as design and execute training programs that develop leadership capabilities of those with supervisory responsibilities.

### 56. Training Schemes Procedure

1/ In accordance with this Regulation Article 55(1) orientation programs shall be conducted by the Office.

2/ Training schemes prepared by the Office for human resource development may beconducted in appropriate institutions, locally or abroad, all in all or incollaboration with these institutions, as the case may be.

### 57. Obligation of Trainee Public Prosecutor

Any public prosecutor shall:

1/ Participate with full consent in the appropriate training schemes designed by the Office;

https://chilot.me



፪/ በመሥሪያ ቤቱ ውሳኔ ለስልጠና የተላከበትን የስልጠና ዘርፍ ወይም የሙያ መስክ ለመቀየር፣ ለማቋረጥ ወይም ለማራዘም ሲፈልግ መሥሪያ ቤቱን በቅድሚያ የማስፈቀድ፣

፫/ በመሥሪያ ቤቱ ድጋፍ የረጅም ጊዜ ስልጠና ወይም ትምህርት ባገኘበት ሙያ ቢያንስ ስልጠናው ወይም ትምህርቱ የወሰደውን ጊዜ እጥፍ ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት የማበርከት ግዴታ አለበት።

## ክፍል አራት

## አገልግሎት ስለማቋረጥና ስለማራዘም

### ፶፰. ሥራን በገዛ ፈቃድ ስለመልቀቅ

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም ጊዜ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመተው ይችላል።

፪/ ሥራን በገዛ ፈቃድ ለመልቀቅ የሚቀርበው ጥያቄ አቃቤ ሕጉ ሥራውን ለማቆም ከሚፈልግበት ቀን አንድ ወር አስቀድሞ በጽሑፍ መቅረብ አለበት፤ ሆኖም ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ የመልቀቅ ጥያቄውን ስለመተዉ በጽሑፍ ከገለጸ በሥራው ላይ እንዲቀጥል መደረግ አለበት።

፫/ በገዛ ፈቃድ ሥራን ለመተው በሚቀርበው ማመልከቻ ላይ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ ፲፭ (አሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ ዐቃቤ ሕጉ ሥራውን እንደሚተው ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ ሥራውን ለመተው እንደተፈቀደለት ይቆጠራል።

፬/ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሥራ ይበደላል ብሎ ካመነ አቃቤ ሕጉ ሥራውን ለማቆም የሚፈልግበትን ቀን ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል።

፭/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በሐኪም ማስረጃ በተረጋገጠ የጤና መታወክ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተመደበበት፣ በተዛወረበት ወይም በተደለደለበት የሥራ ቦታ ለመሥራት ፈቃደኛ ካልሆነ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

2/ Obtain the prior permission of the Office where he desires to change, cease or extend the field of training for which the Office has sent him;

3/ Serve the Office for twice the period of his long term of training period or in the field he has been trained with the support of the Office.

## PART FOUR

## Termination and Extension of a Service

### 58. Resignation

1/ A public prosecutor may resign from service at any time in his free consent.

2/ Notification of resignation in his free consent shall be given in writing at least one month before the resignation is to take effect; however, if he canceled his resignation at any time in writing before the decision of the Attorney General he shall be accepted.

3/ When the decision is not provided within fifteen (15) days upon receiving the notification of resignation in his free consent, it shall be taken as the resignation is permitted from the starting date of notification.

4/ The effective date of the resignation may be postponed by the Attorney General for no longer than one month if the resignation of the public prosecutor is believed to negatively affect the work.

5/ Unless it is certified by medical health certificate, when a public prosecutor is not volunteered to work in his assigned, transferred or deployed work place shall be taken as terminated in his free consent.

https://chilot.me



## ፶፱.በዕድሜ ምክንያት አገልግሎትን ስለማቋረጥ

፩/ ዐቃብያነ ሕግ በጡረታ ከሥራ የሚገለሉበት ዕድሜ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ የተወሰነው ይሆናል፡

፪/ በዕድሜና ዕድሜ ሣይደርስ ጡረታ የሚወጡ አቃብያነ ሕግ መብትና ግዴታ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ በተወሰነው መሠረት ይፈጸማል።

፫/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ስለመንግሥት ሠራተኞች አገልግሎት በሕግ የተወሰነው የዕድሜ ገደብ ከሚፈጽምበት የመጨረሻ ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት ሥራውን እንዲያቆም ይደረጋል።

፬/ አቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው ምክንያት ሥራውን የሚያቆምበትን ቀን ከስድስት ወር አስቀድሞ በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል። የመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሠጠዋል።

## ፷.በሕመም ምክንያት አገልግሎትን ስለማቋረጥ

፩/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳፪(፪) በተደነገገው የሕመም የፈቃድ ጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሥራው ያልተመለሰ ዐቃቤ ሕግ አገልግሎቱ ይቋረጣል፤ ይህም ሲሆን ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ከመጨረሻው የፈቃድ ቀን ጀምሮ አቃቤ ሕጉ ከሥራው እንዲሰናበት ያዛል።

፪/ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ (፭) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት አቃቤ ሕግ ለዘለቄታው መሥራት አለመቻሉ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ አገልግሎቱ ይቋረጣል።

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፮(፪)(ለ) መሠረት በሚፈጸም ዝውውር ተስማምቶ ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆነ ዐቃቤ ሕግ አገልግሎቱ ይቋረጣል።

## 59. Termination of Service Due to Retirement

1/ Retirement age of a public prosecutor shall be determined in accordance with Civil Servants' Pension Law.

2/ The right and duties of a public prosecutor retiring on or before retirement age shall be in accordance with Civil Servants Pension Law.

3/ The retirement of a public prosecutor shall become effective on the last day of the month in which he attains retirement age without special procedure.

4/ A public prosecutor retiring for the reason stated under Sub-article (1) of this Article shall be informed of the retirement in writing (6) six months prior to the date of this retirement. Leave with salary shall provide for the last two (2) months.

## 60. Termination of Service Due to Sickness

1/ Without prejudice toArticle 22(2) of this Regulation,a public prosecutor shall be terminated if there is no prospect of early recovery.If the public prosecutor is no longer fit for service in such a case the Attorney General shall order that the termination be effective on the last day of the sick leave.

2/ Without prejudice to the provision of Article 22(5) of this Regulation, where a public prosecutor who has sustained employment injury is medically determined to be permanently disabled, his service shall forthwith be terminated.

3/ If a public prosecutor does not agree on the transfer that could be undertaken in accordance to Article 36(2)(b) of this Regulation, his service shall be terminated.

https://chilot.me



**፷፩.<u>ዐቃብያነ ሕግ የተመደቡበት የሥራ ደረጃ በመሠረዙ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>**

፩/ አንድ ዐቃቤ ሕግ ተመድቦበት የነበረው የሥራ ደረጃ የተሠረዘ እንደሆነ በነበረው ደረጃ ወደ ሌላ የሥራ ደረጃ ተዛውሮ እንዲሠራ መደረግ አለበት።

፪/ ዐቃቤ ሕጉን በሦስት ወር ውስጥ ወደ ሌላ የሥራ ደረጃ ለማዛወር ያልተቻለ እንደሆነ በሕግ የተወሰኑት ሌሎች መብቶቹ እንደተጠበቁ ሆነው አስቀድሞ የ፫ (የሦስት) ወር ማስጠንቀቂያ ተሠጥቶት ከሥራው ይሰናበታል።

፫/ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት አገልግሎቱ የሚቋረጠው በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ በተመሳሳይ የሥራ ደረጃ ላይ ካሉ ሌሎች አቃብያነ ሕግ ጋር ሲወዳደር በሥራ ውጤቱና ባለው ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም አቃቢተ ሕጓ ነፍሰ ጡር በሆነችበት ጊዜ ወይም ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ከሥራዋ አትሰናበትም።

**፷፪.<u>በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት</u>**

፩/ የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ አቃቤ ሕግ ያለውን እውቀትና ችሎታ እየተጠቀመ በተመደበበት ሥራ ላይ የአፈፃፀም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለሦስት ጊዜ ከሚጠበቀው ውጤት በታች ከሆነ በችሎታ ማነስ ከሥራ ይሰናበታል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም ለ፭ (አምስት) ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ሲያገኝ የነበረ አቃቤ ሕግ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለአራት ጊዜ ከሚጠበቀው ውጤት በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ከሥራ የሚሰናበት አቃቤ ሕግ የ፩ (አንድ) ወር ማስጠንቀቂያ ይሠጠዋል።

**61. <u>Termination of Service Due to Cancellation of Job Grade</u>**

1/ Where the grade to which a public prosecutor was assigned is cancelled, he shall be transferred to another job retaining his previous grade.

2/ Without prejudice to the rights of the public prosecutor under other relevant laws, where the transfer can not be made within three (3) months, he shall be terminated upon being given three (3) months prior notice.

3/ In accordance with Sub-Article (2) of this Article, the public prosecutor's service shall be terminated after ensuring his efficiency and skills are low as compared to the other public prosecutors' service who have similar grade to his through competition.

4/ Notwithstanding to sub-article (2) of this Article, a pregnant public prosecutor during her pregnancy period or four months after birth shall not be terminated.

**62. <u>Termination on Grounds of Inefficiency</u>**

1/ The service of a public prosecutor who has completed his probation period shall be terminated due to inefficiency where his performance evaluation result is below the expected for three successive evaluation periods despite exerting all his knowledge and ability to accomplish his work.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-article (1) of this Article, a public prosecutor whose performance evaluation result is high for five successive years shall not be dismissed on grounds of inefficiency unless his performance result becomes below the expected for the following four successive evaluation periods.

3/ The termination of a public prosecutor under Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be provided one month warning.

https://chilot.me


**፷፫.ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሥራ ማሰናበት**

፩/ የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ ዐቃቤ ሕግ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ ምክንያቱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመሥሪያ ቤቱ ማሳወቅ አለበት።

፪/ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለመሥሪያ ቤቱ ሲያሳውቅ መሥሪያ ቤቱ አቃቤ ሕጉ ከሥራ ገበታው ላይ የተለየበት ምክንያት ከአቅም በላይ መሆኑን ካረጋገጠ አቃቤ ሕጉ ይዞት የነበረውን የሥራ ደረጃ ለስድስት ወር ክፍት አድርጎ መጠበቅ አለበት፤ ሆኖም አቃቤ ሕጉ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራው ካልተመለሰ ከሥራ ማሰናበት ይችላል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ቢኖርም አቃቤ ሕጉ ከስድስት ወር በላይ በሥራ ላይ ያልተገኘው በእስር ምክንያት ከሆነና በተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ስላለመባሉ ማስረጃ ካቀረበ መሥሪያ ቤቱ ባለው ክፍት የሥራ ደረጃ ቀደም ሲል ይከፈለው የነበረውን ደመወዝ እያገኘ ወደ ሥራ እንዲመለስ ማድረግ አለበት።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ አቃቤ ሕግ ባልታወቀ ምክንያት ለተከታታይ አሥር ቀናት ከመደበኛ የሥራ ቦታው ላይ ከተለየ በየአስር ቀናት ልዩነት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ በማስታወቂያ ተጠርቶ ለመሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካላደረገ ከሥራ ይሰናበታል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት በማስታወቂያ ጥሪ የተደረገለት አቃቤ ሕግ ከሥራ ከተለየበት ቀን ጀምሮ አንድ ወር ከመሙላቱ በፊት ወደ ሥራው ለመመለስ ለመሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካደረገ በዲሲፕሊን መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ወደ ሥራው እንዲመለስ ይደረጋል።

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ቢኖርም ከሥራ የተሰናበተ ዐቃቤ ሕግ ከሥራ ከቀረበት ቀን

**63. Termination due to Force Majeure Situations**

1/ A public prosecutor who has completed probation and is absent from work due to force majeure, shall inform the situation within one month to the Office.

2/ The Office that has received the reasons of absence of public prosecutor in accordance with sub-article (1) of this Article shall, after verifying the validity of the reason, keep the post of the public prosecutor vacant for six months. Provided, however, that the service of a public prosecutor may be terminated if he is unable to resume work within the six months.

3/ Notwithstanding to sub-article (2) of this Article, if a public prosecutor who is absent from work due to detention for more than six months produces an evidence of his acquittal, the office shall reinstate him on any vacant position by maintaining his previous salary.

4/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, when a public prosecutor who has completed his probation is absent from his work for ten consecutive workings days due to unknown reasons the Office may terminate the employment after calling him in two notices in ten days interval.

5/ A public prosecutor who responded to the notices made in accordance with Sub-Article (4) of this Article within a month from the first day of absence, without prejudice s to a disciplinary request the Attorney General shall reinstate him to his job.

6/ Notwithstanding to the Provisions of Sub-Article (4) of this Article, the Attorney General may reinstate the public

https://chilot.me



ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከሥራ የቀረበት ምክንያት ከአቅም በላይ ለመሆኑ ለመሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካደረገና በቂ ማስረጃ ካቀረበ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ ደረጃ ከተገኘና ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ሲፈቅድ ወደ ሥራ ሊመለስ ይችላል።

፯/ የሙከራ ጊዜውን ያላጠናቀቀ ዐቃቤ ሕግ ባልታወቀ ምክንያት ለአንድ ወር ጊዜ በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ ያለተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቱ ይቋረጣል።

**፷፬.በዲሲፐሊን ምክንያት ከሥራ ስለመሰናበት**

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፡-

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፰(፪)(ረ) መሠረት የዲሲፕሊን ቅጣት የተወሰነበት እና

፪/ ይግባኝ ሳይጠይቅ የይርጋ ጊዜው ያለፈበት ወይም ይግባኝ ጠይቆ ቅጣቱ ያልተሠረዘለት ከሆነ

ከሥራ ይሰናበታል።

**፷፭.በሞት ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ**

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከሞተበት ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ የሚቋረጥ ሲሆን በሞት ምክንያት አገልግሎት ሰለሚቋረጥ ሰራተኛ የጡረታ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**፷፮.አገልግሎት የሚቋረጥባቸው ሌሎች ምክንያቶች**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፫) የተዘረዘሩት ከዐቃቤ ሕግነት ሙያ የሚከለክሉ ምክንያቶች መካከል የአንዱ መኖር አገልግሎትን ያቋርጣል።

**፷፯.የሥራ ልምድ ማስረጃ**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በሥራ ላይ እያለ ወይም አገልግሎቱ ከተቋረጠ በኋላ በማናቸውም ጊዜ የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሠጠው ሲጠይቅ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑን እና ሲከፈለው የነበረውን ወርሀዊ ደመወዝ የሚገልጽ የሥራ ልምድ ማስረጃ ይሠጠዋል።

prosecutor to his job if the public prosecutor applies for his job within six months after the termination of his employment and produces sufficient evidence to prove that his reasons of absence was due toforce majeure and there exists a similar vacant position within the office.

7/ The service of a public prosecutor who has not completed his probation shall be terminated without any additional formality, where he is absent from work for one month due to unknown reasons.

**64. Termination of Service on Disciplinary Grounds**

The service of a public prosecutor shall be terminated where:

1/ a disciplinary penalty under Article 88(2)(f) of this Regulation is imposed on him; and

2/ time expired without requesting appeal or the penalty is not revoked on appeal.

**65. Termination on the Ground of Death**

The Service of a public prosecutor shall be terminated on the day of his death and the provisions of pension law shall be applied.

**66. Termination of Service on other Grounds**

The Presence of one of the prohibitions from a public prosecutor profession stated in Article 4(3) of this Regulation shall terminate the prosecutor’s service.

**67. Certificate of Service**

1/ Where the public prosecutor is on service or terminated for any reason, where he so requests,he shall be provided with a certificate of service indicating the type and duration of service as well as his salary.

https://chilot.me


፪/ የሥልጠና ውል ግዴታ ወይም በመሥሪያ ቤቱ የሚፈለግበት ማናቸውም ዕዳ ያለበት አቃቤ ሕግ በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ የውል ግዴታውን ስለመፈጸሙ ወይም ከዕዳ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከማግኘቱ በፊት የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት አይሰጠውም።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በሥራ ላይ እያለ የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ለሚጠይቅ አቃቤ ሕግ ተፈጻሚ አይሆንም።

**፷፰.አገልግሎትን ስለማራዘም**

፩/ የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ ዐቃቤ ሕግ የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ ከአምስት አመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱ ሊራዘም ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የአንድን አቃቤ ሕግ አገልግሎት ማራዘም የሚቻለው:-

ሀ) የዐቃቤ ሕጉ ትምህርት፣ ልዩ ዕውቀትና ችሎታ ለመሥሪያ ቤቱ ሥራ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ) በሹመት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ተተኪ ዐቃቤ ሕግ ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

ሐ) ሠራተኛው ለሥራው ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

መ) የጀመረውን ሥራ እዲያጠናቅቅ፣

ሠ) ሠራተኛው አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ፣ እና

ረ) የአገልግሎቱ መራዘም የመጦሪያ ዕድሜው ከመድረሱ ከሦስት ወር በፊት በዋና ጉባኤው ለጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ቀርቦ ሲፈቀድ፣

ነው።

2/ Where the public prosecutor is terminated with duties of training contract or any other loan needed by the Office shall not be provided a certificate of service before getting clearance.

3/ Where the public prosecutor is on service, where he so requests a certificate of service, shall not be applicable to Sub-article (2) of this Article.

**68. Extension of Service**

1/ The service of a public prosecutor who has completed his probation may be extended beyond his retirement age for a period not exceeding five years.

2/ The service of a public prosecutor may be extended beyond his retirement age under Sub-article (1) of this Article where:

a) he is found very essential for the office with his education, special knowledge and skill;

b) it is ensured unable to get substitution of a public prosecutor with an appointment; transfer or employment;

c) his health condition is certified by medical certificate;

d) it is found necessary to complete the work he has been doing;

e) he has agreed to the extension of his service; and,

f) the extension is allowed by the Attorney General before three (3) months of the retirement upon recommendation by the Commission.

https://chilot.me



## ክፍል አምስት

## ስለ ዐቃብያነ ሕግ ግዴታ

**፷፱.ስለ ታማኝነት**

፩/ ዐቃብያነ ሕግ በሥራ ነጻነታቸው የተጣለባቸውን እምነት መጠበቅ አለባቸው።

፪/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ መላ ጉልበቱን፣ ሀሳቡንና ችሎታውን በታማኝነት ለመንግሥትና ለሕዝብ አገልግሎት ጥቅም ማዋል አለበት።

**፸.ስለ ዐቃቤ ሕግ ጠባይ**

ማንኛውም አቃቤ ሕግ፡-

፩/ የሕዝብን አክብሮትና እምነት እንዲያገኝ በመሥሪያ ቤቱም ሆነ ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ በማናቸውም ጊዜ መልካም ጠባይና ሥነ ምግባር እንዲኖረው ያስፈልጋል።

፪/ በማንኛውም ጊዜ የሙያውን ክብር ለማስጠበቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ አሟልቶ መገኘት አለበት።

**፸፩.ስለ ታዛዥነት**

፩/ ማንኛውም አቃቤ ሕግ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፮(፪) (ለ) ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተመደበበት፤በተዛወረበት ወይም በተደለደለበት ቦታ የመሥራት ግዴታ አለበት።

ለ) የተመደበበትን መደበኛ ሥራና ሌላውንም ተመሳሳይ ሥራ ባለው ዕውቀትና ችሎታ ሁሉ መፈፀም አለበት።

፪/ ዐቃቤ ሕጉ ከቅርብ ሃላፊ ወይም ከበላይ ኃላፊው የሚሠጠው ትዕዛዝ በግልጽ ከሕግ ውጭ ካልሆነ በቀር እንደትዕዛዙ መፈጸም አለበት፤ በማናቸውም አኳኋን የቅርብ ሃላፊ ወይም የበላይ ሃላፊ ለሚሠጠው ትዕዛዝ ሕጋዊነት ተጠያቂ ነው።

፫/ ዐቃቤ ሕጉ የቅርብ ሃላፊው ወይም የበላይ ኃላፊው የሰጠው ትእዛዝ በጽሑፍ እንዲሰጠው የጠየቀ እንደሆነ ትእዛዙ በጽሑፍ እንዲሰጠው መደረግ አለበት።

## PART FIVE

## Obligation of Public Prosecutors

**69. Loyalty**

1/ Public prosecutor shall keep their duties of working independency;

2/ Any public prosecutor shall devote his whole energy and ability to providing loyal service in the interest and for the benefit of the government and the public.

**70. Personal Conduct of a Public Prosecutor**

1/ Any public prosecutor shall at all times exhibit good behavior and conduct within and outside the Office in order to win the respect and confidence of the public.

2/ He shall, at all times, fulfill whatsoever is required of him to protect the dignity of his profession.

**71. Obedience**

1/ Any public prosecutor:

a) In accordance with Article 36(2) (b) or unless without good cause shall perform all his duties which he has been assigned, transferred or deployed;

b) shall perform his all duties which he has been assigned regular and other related duties to his best knowledge and ability.

2/ A public prosecutor shall obey the orders of his immediate official or superior unless it is clearly contrary to the law. In all cases the immediate official or superior is responsible for the legality of his orders.

3/ When a public prosecutor requested order in writing, an immediate official or superior shall provide.

https://chilot.me


**፸፪.ስለ ገለልተኛነት**

ዐቃብያነ ሕግ፡-

፩/ የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይም በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሳተፍ ወይም በሥራቸው ላይ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን መግለጽ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ ማሳየት የተከለከለ ነው።

፪/ በማናቸውም ሁኔታ በሥራቸው ላይ የግል እምነታቸውን ወይም ኃይማኖታቸውን የሚያንጸባርቅ ተግባር መፈጸም የለባቸውም።

**፸፫.ዐቃቤ ሕግ ከሕዝብ ጋር ስላለው ግንኙነት**

ዐቃቤ ሕግ፡-

፩/ ያለፍራቻ፤ ያለአድልኦ ወይም ያለምንም ጥላቻ በተለይም ከግለሰባዊና ከወገናዊ ጥቅም ወይም ከሕዝባዊና ከመገናኛ ብዙሃን ግፊት ተጽእኖ ሳያድርበት የሕዝብን ጥቅም ብቻ በማስቀደም ተግባሩን ማከናወን አለበት።

፪/ ምን ጊዜም የሰዎችን ሰብአዊ መብትና ክብር ማክበር፣ መጠበቅና መደገፍ አለበት።

**፸፬.ምስጢር ስለመጠበቅ**

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፡-

፩/ መረጃው ተራ ወይም በሕዝብ ዘንድ የታወቀ ካልሆነ ወይም መደበኛ ሥራውን በሕጋዊ መንገድ ለመፈጸም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር በሥራው አጋጣሚ ወይም ምክንያት ወይም በሌላ አኳኋን ያገኘውን መረጃ ለማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም።

፪/ በሕግ ሥልጣን በተሠጠው አካል ወይም ኃላፊ በአግባቡ ካልታዘዘ በስተቀር በአሠራር ምስጢር የተባሉትን መረጃዎች፣ ቃለ ጉባኤዎች፣ የሥራ ዕቅዶችና እነዚህን የመሳሰሉትን ምስጢራዊ ጉዳዮች ሁሉ በሥራም ላይ ሆነ ከሥራ ውጭ ለሌላ ማናቸውም ሰው መግለጽ የለበትም።

**፸፭.ገንዘብ ስለመበደር**

፩/ አዘውትሮ ገንዘብ መበደር ክልክል ነው።

፪/ ዐቃቤ ሕግ በሥራው ምክንያት ከሚያጋጥመው

**72. Impartiality**

Public prosecutors:

1/ to be a member of political parties or make participation or reflecting political outlook in their duties or reflecting in any other means are prohibited;

2/ shall not reflect personal belief or religion in their duties under no circumstances.

**73. Public prosecutor's Relations with the Public**

A public prosecutor:

1/ shall always perform his duties without fear, fever, or any disgust especially from private and unfair interest or impacts public and mass media impact bear in mind that his actions concern the interest of the public;

2/ shall respect, support and keep human rights and human dignity.

**74. Secrecy**

Any public prosecutor:

1/ shall not disclose to any person any information gained in the course of his official duties or otherwise except to the extent that such disclosure is necessary for the discharge of his lawful duty,unless such information is of minor importance or is a public knowledge;

2/ shall not disclose in the discharge of his duties or otherwise, information, proceedings, minutes, plans or similar classified matters, which, ,in accordance with practice have been declared confidential, to any person except by the order of supreme or unless such other person is legally permitted to know such matters.

**75. Borrowing Money**

1/ Persistent borrowing is prohibited.

2/ a public prosecutor is strictly prohibited from borrowing or attempting to borrow money from a member of the

https://chilot.me


ባለጉዳይ ገንዘብ ለመበደር መሞከር ወይም መበደር ፍፁም ክልክል ነው::

**፸፮.ስጦታዎች**

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከሥራው ጋር በተያያዘ ለሠጠው ወይም ወደፊት ስለሚሠጠው አገልግሎት ከማንኛውም ሰው ማናቸውም ዓይነት ዋጋ ያለውም ሆነ የሌለው ስጦታ መጠየቅ ወይም መቀበል የለበትም።

**፸፯.በመንግሥት ሥራና በግል ጉዳዮች ወይም ጥቅሞች መካከል ስለሚፈጠር ግጭት**

፩/ ማናቸውም ዐቃቤ ሕግ የራሱ፣ የዘመዶቹ ወይም የወዳጆቹ የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከሥራው ወይም በሥራው ምክንያት ከያዘው የሕዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ለቅርብ ኃላፊው ወዲያውኑ በማሳወቅ ጉዳዩ በሌላ አቃቤ ሕግ እንዲታይ ማመልከት አለበት።

፪/ ጉዳዩ የቀረበለት የቅርብ ሃላፊም ማመልከቻውን መርምሮ እውነት መሆኑን ካረጋገጠ ጉዳዩ በሌላ ዐቃቤ ሕግ እንዲታይ ማድረግ አለበት።

**፸፰.ስለግል ደብዳቤዎች**

፩/ ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ አድራሻ የግል ደብዳቤ ሊጽፍ ወይም ሊፃፍለት ይችላል፤ ለመላላክ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚመለከተው ዐቃቤ ሕግ መክፈል አለበት።

፪/ በመሥሪያ ቤቱ አድራሻ የተላከ የማንኛውም አቃቤ ሕግ ደብዳቤ፣ እሽግ ወይም ዕቃ ቢጠፋ መሥሪያ ቤቱ በኃላፊነት አይጠየቅም።

**፸፱.በመሥሪያ ቤቱ መገልገያዎች ስለመጠቀም**

፩/ ዐቃብያነ ሕግ ሥራቸውን በሚገባ ለመፈጸም ያህል ብቻ በመሥሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ መገልገያዎች መጠቀም ይችላሉ።

፪/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ለሥራ ማከናወኛ በተሰጡት መሣሪያዎችና መገልገያዎች ላይ በሚደርስ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በአቃቤ ሕጉ

public with whom the public prosecutor has a contact in discharge of his official duties.

**76. Gifts**

Any public prosecutor shall not solicit or take remuneration or consideration in whatever form from any person in respect of services rendered or expected to be rendered.

**77. Conflict of Duty and Private Interest**

1/ Any public prosecutor shall forthwith report to his immediate official a case in which his interest or his relative's or friend's interests conflict with his duties and shall request that the case be handled by another public prosecutor.

2/ The immediate official shall make decision to handle the case by another public prosecutor after investigating the request.

**78. Private Correspondence**

1/ Public prosecutors may send or receive private correspondences through the Office's address. All expenses arising there from shall be borne by the public prosecutor.

2/ The Office may not be held responsible for the loss of any private letter, parcel or items sent via its address.

**79. Use of Office Equipment**

1/ Public prosecutors may utilize office equipment only to the extent necessary to accomplish their work appropriately.

2/ Any public prosecutor shall be liable for office equipment damage if the fault is made intentionally or by negligence.

https://chilot.me


ቸልተኝነት ወይም ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው።

**፹.ለሌላ ስለመሥራት**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ፦

ሀ/ በአግባቡ ሲታዘዝ ከሦስት አመት ለማይበልጥ ጊዜ ለሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት ልማት ድርጅት ወይም አለም አቀፍ ድርጅት መሥራት አለበት።

ለ) ለመሥሪያ ቤቱ የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ለተሠጠው ሥራና ኃላፊነት ተቃራኒ የሆነ ወይም ከሥራውና ከሀላፊነቱ ወይም ከሙያ ሥነ-ምግባር ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም የውጭ ሥራ ሊሠራ አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ከሥራ ሰዓት ውጭ ለፈጠራ፣ ለኪነ ጥበብ፣ ለጥናትና ምርምር፣ የሕግ ረቂቆችን ለማዘጋጀት፣ ለሳይንሳዊና ለትምህርታዊ ሥራ ካልሆነ በስተቀር የውጭ ሥራ ለመሥራት በቅድሚያ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉን ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፫/ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ታዝዞ ሲሰራ የተሻለውን ደመወዝና ሌላ ጥቅማጥቅም የማግኘት መብት አለው።

፬/ ከዐቃቤ ሕግነት ሙያ ጋር የማይጣጣም የሥራ ዝርዝር መመሪያ ይወሰናል።

**፹፩.ስለአለባበስ**

ዐቃቤ ሕግ በሥራ ላይ እያለ በሕግ የሚደነገገውን የአለባስ ሥርዐት ማክበር አለበት።

**ክፍል ስድስት**

**የዐቃብያነ ሕግን የግል ማሕደር ስለማደራጀት**

**፹፪.ስለአቃቤ ሕግ የግል ማሕደርና ካርድ**

፩/ መሥሪያ ቤቱ ለእያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ ማሕደርና የተለየ የግል ካርድ እንዲኖረው

**80. Working for Others**

1/ Any public prosecutor:

a) shall undertake to work for other governmental offices or public enterprises or international organizations upon receiving appropriate order for not more than three years.

b) shall not undertake any outside activity which would in any way impair his service or which in any way conflicts with his duties or is inconsistent with his position and profession as a public prosecutor.

2/ Without prejudice to sub Article (1) of this Article, any public prosecutor shall obtain prior permission of the Attorney General to undertake any outside activity except for art, creativity, studies and researches, drafting laws, and scientific and educational activities.

3/ A public prosecutor shall have right to get better salary and other benefits when he is working upon receiving the appropriate order in accordance with Sub-article (1) (a) of this Article.

4/ Details activities inconsistent with professions of public prosecutorሰ shall be determined by a directive.

**81. Dressing Manner**

Public prosecutor shall respect the regulated dressing manner on his duties.

**PARTSIX**

**Personal Records of Public Prosecutors**

**82. Personal File and Personal Card**

1/ The Office shall keep for any public prosecutor a personal file and a separate personal card.

https://chilot.me



ማድረግ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ፩ መሠረት የሚደራጀው የግል ማሕደር፡-

ሀ) የአቃቤ ሕጉን የቅጥር ማመልከቻ፣ የተቀጠረበትን ደብዳቤና የፈፀመውን ቃለ መሐላ፣

ለ) የጤንነት ምርመራ ውጤት ማስረጃ፣

ሐ) ከወንጀል ቅጣት ነጻ ለመሆኑ ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የተሰጠ ማስረጃ፣

መ) የትምህርት እና የቅድመ ሥራ ሥልጠና ወይም እንደአስፈላጊነቱ የልዩ ሥልጠና ማስረጃ፣

ሠ) ያሳተመው ሙያዊ ወይም የምርምር ጽሑፍ ካለ የሕትመቱ ርዕስ፣ የታተመበት ሁኔታ፣ አሳታሚውና የታተመበት ዓመት ምሕረት፣

ረ) ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ ላገለገለበት ዘመን የተሠጠው የሥራ ምስክር ወረቀት

ሰ) የተሾመበትን የተመደበበትን ወይም የተዛወረበትን ደብዳቤ፣

ሸ) የደሞዝ ጭማሪ የተፈቀደበትን ደብዳቤ፣

ቀ) የዓመት እረፍት ፈቃድ የጠየቀበትና ያስፈቀደበትን ማመልከቻ፣ የሕመም ፈቃድ ወይም ሌላ ፈቃድ ያገኘበትን ማስረጃ ወይም ጽሑፍ፣

በ) የሥራ አፈፃጸም ዘገባ፣

ተ) በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የተሠጠ ውሳኔንና እርምጃ የተወሰደበት ጽሑፍ፣

ቸ) ከሥራ የተሰናበተበት ደብዳቤና እነዚህን የመሳሰሉትን ሌሎች መረጃዎች ሁሉ እንደጉዳዩ ሁኔታ ዋናውን ቅጂ ወይም ግልባጩን መያዝ አለበት።

፫/ የዐቃቤ ሕጉ የግል ካርድ ከዐቃቤ ሕጉ የግል ማሕደር የተለቀሙ ዋና ዋና ጉዳዮችና መረጃዎች ብቻ የሚመዘገቡበት ይሆናል።

**፹፫. የግል መረጃዎችን ስለመመርመር**

፩/ ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በመሥሪያ ቤቱ

2/ The personal file established under sub Article (1) of this Article shall consist:

a) the public prosecutor’s application for work, the letter of employment and the oath;

b) medical certificate;

c) certificate from the Federal Police Commission that which shows that he is free from criminal penalty;

d) educational and pre service training or special training certificate as may be necessary;

e) published professional or research paper if any; topic, conditions of printing, publisher and printing year;

f) certificate of service rendered outside the Office;

g) letter of appointment,assigned or transferred;

h) notifications of increments of salary;

i) applications and certificates for leave, sick leave or other leave;

j) efficiency reports;

k) letter of disciplinary measures;

l) Letter of dismissal; and other similar information of original or copies, as the case may be.

3/ The personal card of a public prosecutor shall contain the most important data and information about the prosecutor.

**83. Examination of Personal Records**

1/ Any public prosecutor has the right to examine his

https://chilot.me



በሚገኘው የግል ማሕደሩ ውስጥ የተቀመጡ መረጃዎችን ጠይቆ ለማየትና ለመገልበጥ መብት አለው፡፡

personal file upon request and to make copies there of.

፪/ የመሥሪያ ቤቱ የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ዋና ጽሕፈት ቤት ሀላፊ ወይም የዐቃብያነ ሕግ የግል ማሕደርና ካርድ አከናዋኝ ካልሆነ በቀር፣ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ወይም ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ የሚገኙ ሌሎች ሰዎች የአንድን ዐቃቤ ሕግ የግል ማሕደር መመርመር የሚችሉት ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ በጽሑፍ ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡

2/ Persons other than the head office of public prosecutors' administration council, public prosecutors' administration officer and the record clerk for public prosecutors, either from within or outside the Office, may examine the personal file of a prosecutor only with written permission of the Attorney General.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ለዐቃቤ ሕጉ የተፈቀደውን መብት በመቃረን ወይም በማጓደል ማናቸውንም በዐቃቤ ሕጉ የግል ማሕደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ የሚገባውን ማስረጃ ወይም መረጃ እንዳያይ አድርጎ ማስቀመጥ ወይም ዐቃቤ ሕጉን ለመጉዳት ወይም ለመጥቀም በማሰብ እንዲህ ያለውን ማስረጃ ወይም መረጃ ከግል ማሕደር ውስጥ ማውጣት ክልክል ነው፡፡

3/ Keeping the personal file of a public prosecutor in a manner that prejudices the right of the public prosecutor stated in sub Article (1) of this Article or detaching a document from the personal file with the intention to either cause damage or benefit the public prosecutor is prohibited.

፬/ የዐቃቤ ሕጉ የጤንነት ምርመራ ውጤት ማስረጃ፣ በልዩ ማሕደር እንዲቀመጥ መደረግ አለበት፡፡

4/ Medical reports of a public prosecutor shall be kept in a special file.

፭/ አዐቤ ሕጉ ሳያውቀው በግል ማሕደሩ ውስጥ ማንኛውንም ማስረጃ ማስቀመጥ ክልክል ነው፡፡

5/ It is prohibited to maintain any information in the personal file of a public prosecutor without his knowledge.

## ክፍል ሰባት
## ስለዲስፐሊን
### ንዑስ ክፍል አንድ
### መርሕ

## PART SEVEN
## Discipline
### Section One
### Principle

**፹፬.ስለዲሲፕሊን ቅጣት አላማና አፈፃፀም**

፩/ የዲሲፕሊን ቅጣት መሠረታዊ ዓላማ ዐቃቤ ሕጉ በፈፀመው ጥፋት ተጸጽቶ እንዲታረምና ወደፊት በብቃት ሥራውን ለማከናወን እንዲችል ለማስተማርና እንዲሁም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

፪/ ሥራውን ችላ የሚል ወይም የማይፈጽም ወይም

**84. Objective and Enforcement of Disciplinary Measures**

1/ The basic objective of a disciplinary measure is to correct the public prosecutor committing an offense and to educate him to perform his duties efficiently and to dismiss him if the corrective measures fail.

2/ A public prosecutor who derelicts or fails to perform his

https://chilot.me



ማንኛውንም የዲሲፕሊን ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት የሚፈጽም ዐቃቤ ሕግ ስለጥፋቱ በፍትሐብሔር ወይም በወንጀል የሚኖርበት ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መሠረት የሚወስኑ ቅጣቶች ይፈፀሙበታል።

፫/ በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የሚወሰነው ቅጣት ማናቸውም ፍርድ ቤት የሚሠጠውን ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊፈፀም ይችላል።

**፹፭.ስለዲሲፒሊን ጥፋቶች**

፩/ የሚከተሉት ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

ሀ) ጉቦ መቀበል፣ መጠየቅ፣ወይም ለሌላ ሰው እንዲሰጥ ማድረግ፣

ለ) ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ፣ በአማላጅ ወይም በማዳላት መሥራት፣

ሐ) ራስን ወይም ሦስተኛ ወገንን ለመጥቀም በጽሑፍ የሠፈረ ማስረጃን ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ማስረጃ መጠቀም፣

መ) ከባለጉዳይ ገንዘብ መበደር፣

ሠ) አግባብ ያለውን ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለሚመለከተው ባለማሳወቅ ወይም በመደበቅ የውሳኔው ሁኔታ እንዲዛባ ማድረግ፣

ረ) ያለበቂ ምክንያት ሥራን ማዘግየት ወይም ባለጉዳይን ማጉላላት፣

ሰ) አእምሮን የሚያደነዝዝ ወይም ሱስ የሚያስይዝ ዕጽ መጠቀም ወይም ልዩ ፈቃድ ሳይኖረው የሚያደነዝዝ ወይም ሱስ የሚያስይዝ መድሐኒት መጠቀም፣

ሸ) ሰክሮ በሥራ ላይ መገኘት ወይም በአደባባይ በመታየት ወይም በመጠጥ ቤቶች ውስጥ ሁከት ወይም ጸብ በማንሳት የሙያውን ሥነ-ምግባርና የመሥሪያ ቤቱን ክብር ማጉደፍ፣

ቀ) የምርመራ ወይም የዐቃቤ ሕግ መዝገብ መጣል ወይም መሠወር ወይም በቂ ማስረጃ

duties, or commits any other breach of discipline or ethics shall be liable to the measures under this Regulation without prejudice to any civil or criminal liability.

3/ Disciplinary measures may be taken for breaches of discipline or for any other offence irrespective of any court action or proceedings.

**85. Disciplinary Offenses**

1/ The following are serious disciplinary offenses:

a) taking or soliciting bribes or to facilitate ways to be given to others;

b) doing favor through intermediaries with intent to obtain unlawful benefit for himself or for another;

c) falsification of written documents or to make use of falsified evidence to obtain benefit for himself or for a third party;

d) borrowing money from the public;

e) creating a situation which leads to an improper decision through negligently or intentionally failing to inform or concealing relevant information or points;

f) creating inconvenience to the public by delay of service without good cause;

g) consumption of narcotic drugs or other substances of such a nature or use narcotic drugs or other substances of such a nature without special permission ;

h) found drunk in office or at public place or initiating violence or obstruction in drinking houses thus harming the reputation of the office and the profession;

i) to abandon or conceal investigation or public prosecutor's files, or closing files having sufficient

https://chilot.me


እያለ ክስ አለማቅረብ ወይም በእርቅ መነሳት የማይገባውን ክስ ማንሳት ወይም መከሰስ የማይገባውን ሰው አላግባብ መክሰስ፣

በ) በሥራ ቦታ ለሞራልና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፣

ተ) ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በመሥሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፣

ቸ) በጽሑፍ ወይም በቃል ከመሥሪያ ቤቱ ወይም ከቅርብ ሃላፊው ወይም ከበላይ ኃላፊው የተሠጠውን ግልጽና ሕጋዊ ትዕዛዝ አለመቀበል ወይም ተግባራዊ አለማድረግ፣

ነ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፩(፫) ላይ የተደነገገውን መተላለፍ፣

ኀ) በጥላቻ ወይም ያላግባብ ዐቃቤ ሕግን በዲስፕሊን መክሰስ፣

ኘ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፯(፩) እና ፩፻፫ (፭) ላይ የተደነገገውን መተላለፍ፣

አ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፪ የተደነገገውን መተላለፍ፣

ኸ) ቀላል የዲስፕሊን ጥፋትን ደጋግሞ መፈፀም፣

ወ) በሥራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈፀም፣

ዐ) በሥራው ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማሳየት፣

ዘ) ማስረጃውና ጭብጡ ግልጽ ሆኖ ሳለ ከጉዳዩ ጋር የማይጣጣም የሕግ አንቀጽ በመጥቀስ ክስ መመሥረት፣

ዠ) በሥልጣን አላግባብ መጠቀም፣

የ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፬ የተደነገገውን መተላለፍ፣

ደ) ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በስምምነት መሥራት ባለመቻል ሥራን መበደል ወይም በሥራ ቦታ ሁከት ማንሳት፣ መደባደብ ወይም ባለጉዳይን መሳደብ፣ ማንጓጠጥ ወይም ክብራቸውን መንካት፣

evidences or withdrawal of charges illegally or framing charges on innocent persons ;

j) committing any act against moral and goodbehavior at work place;

k) damaging office property intentionally or with gross negligence;

l) rejecting or refusing to execute a clear andlawful order given orally or in writing by the Office or his immediate official or superior;

m) contravening provisions of Article 71(3) of this Regulation;

n) improper or hatred disciplinary charges of public prosecutor;

o) contravening provisions of Article 77(1) and 103(5) of this Regulation;

p) contravening provisions of Article 72 of this Regulation;

q) committing simple disciplinary offences repeatedly;

r) to commit sexual harassment or abuse at work;

s) not showing effort and diligence at work;

t) framing charges under an unfit article despite the presence of precise evidences or issues;

u) abuse of power;

v) contravening provisions of Article 74 of this Regulation;

w) obstructing the smooth execution of work by not cooperating with colleagues, or initiating disturbances at work places or quarreling with others or neglecting or degrading clients;

https://chilot.me



ሸ) በቂ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል ባለማድረግ በሥራና በባለጉዳዮች ላይ በደል እንዲደረስ ማድረግ፣

ገ) የዲሲፕሊን ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታን ተከታሎ እርምጃ አለመሰድ ወይም እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል አለማሳወቅ ወይም መደበቅ ወይም፣

ጠ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ከባድ ጥፋቶች።

፪/ የሚከተሉት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

ሀ) ያለ ፈቃድ ከሥራ መቅረት፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹(፪) የተደነገገውን መተላለፍ፣

ሐ) አዘውትሮ መበደር፣

መ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፩ ላይ የተደነገገውን መተላለፍ ወይም

ሠ) ያለ በቂ ምክንያት መሥሪያ ቤቱ በሚያዘጋጀው ወይም እንዲሳተፍ ከተላከበት አስገዳጅ ሥልጠና፣ ዐውደ ጥናት፣ የምክክር መድረክ ወይም በመሳሰሉት ላይ አለመሳተፍ፣

ረ) በሠራተኞች መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር ማድረግ ወይም የሥራ ባልደረባን በሐሰት መወንጀል፣

ሰ) በስብሰባ ወይም በውይይት ወቅት ሐሳብ የሚሰጡ ሰዎችን መስደብ፣ክብራቸውን መንካት፣ማዋረድ፣ወይም የስብሰባ መድረክን ማወክ ወይም ስብሰባን ያለበቂ ምክንያት አቋርጦ መውጣት፣

ሸ) ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ቀላል ጥፋቶችን መፈጸም።

**፹፮.ስለ ሥነ-ሥርዐት ሕግ**

የዲሲፕሊን ክስና ይግባኝ፡-

፩/ በዚህ ደንብ እና

፪/ በዚህ ደንብ ያልተሸፈነ ጉዳይ ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ

x) affecting work and clients by failing to implement a supervision and monitoring activities;

y) failure to take measures on applications relating to disciplinary faults or unable to report disciplinary faults to the relevant organ or concealing it;

z) committing such other similar serious offences.

2/ The following are simple disciplinary offenses:

a) absence from work without leave;

b) contravening provisions of Article 80(2) of this Regulation;

c) persistent borrowing;

d) contravening provisions of Article 81 of this Regulation;

e) refusing to participate or interrupting a training or a work shop facilitated by the Office without justifiable reasons; or

f) inciting conflicts among the workers or initiating false allegations on fellow workers;

g) discouraging or degrading dignity of the participants of meeting or session or obstructing a meeting or leaving from a meeting arbitrarily;

h) committing such other related offences of simple nature.

**86. Procedure**

Disciplinary charges and appeal shall be directed:-

1/ by this Regulation; and

2/ by Criminal Procedure Code for cases not covered in this Regulation

https://chilot.me


መሠረት ይመራል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለዲሲፕሊን ጥፋት፣ ቅጣትና ቅጣትን የመወሰን ሥልጣን

### ፹፯.በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ስለሚወሰኑ ቅጣቶች

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፭ ሥር የተዘረዘሩትን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶችን በመፈፀሙ በዲስፕሊን የተከሰሰ ዐቃቤ ሕግ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው፡-

ሀ) የዲስፕሊን ጥፋቱ ያስከተለው የጉዳት መጠን፣

ለ) የዲሲፕሊን ጥፋት ፈፃሚውን የሀላፊነት ደረጃ፣

ሐ) የዲሲፕሊን ጥፋቱ የተፈጸመበትን አኳኋን፣

መ) የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጻሚው የቀድሞ የሥራ አፈጻጸምና ሥነ ምግባር፣

ሠ) ደጋጋሚነትን እና

ረ) ሌሎች መሰል ሁኔታዎችን

ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

፪/ ዐቃቤ ሕጉ በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንደጥፋቱ ክብደት፡-

ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ፣

ለ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣

ሐ) ተጣርቶ ከሚደርሰው ደመወዙ አንድ ሦስተኛ ካልበለጠ በስተቀር በሁለት ወር ውስጥ የሚከፈል ከቅጣቱ አስቀድሞ ለመጨረሻ ጊዜ ከተከፈለው ደመወዝ እስከ አሥራ አምስት ቀን የሚደርስ የደመወዝ መቀጮ፣

መ) ተጣርቶ ከሚደርሰው ደመወዙ አንድ ሦስተኛ ካልበለጠ በስተቀር በአንድ አመት ውስጥ የሚከፈል ከቅጣቱ አስቀድሞ ለመጨረሻ ጊዜ ከተከፈለው ደመወዝ እስከ

## Section Two
## Disciplinary Offenses, Penalties and Power to Decide

### 87. Disciplinary Penalties

1/ A charge brought against a public prosecutor for a breach of discipline as provided under Article 85 of this Regulation or other similar offences shall be decided by the following taking into consideration:

a) impacts of the disciplinary offence;

b) grades of the person who committed the disciplinary offence;

c) conditions of the committed disciplinary offence;

d) efficiency and conducts of the person who committed the disciplinary offence;

e) persistency; and,

f) other similar conditions.

2/ Where a public prosecutor is found guilty of disciplinary offense he has been charged with, the following penalties may be imposed according to the gravity of the offense:

a) an oral warning;

b) a written warning;

c) a fine not exceeding fifteen (15) days last salary to be paid in two (2) months unless net salary is not exceeding one third of the total;

d) a fine not exceeding three (3) months last salary to be paid in one (1) year unless net salary is not exceeding one third of the total;

https://chilot.me



ሦስት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፣

ሠ) ለሁለት ተከታታይ አመታት አንድ ደረጃ ዝቅ የማድረግ ወይም ለሹመት ብቁ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ተከታታይ አመታት አንድ ደረጃ ከፍ እንዳይል የማድረግ፣

ረ) ከሥራ የማሰናበት ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሠ) መሠረት ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ በማድረግ ወይም ከፍ እንዳይል የተቀጣ ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ፡-

ሀ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ ደረጃ ወይም ባይቀጣ ኖሮ ሊደርስበት ከሚችለው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ ክፍት የሥራ ደረጃ ካለ ያለምንም ተጨማሪ የሹመት ሥነ-ሥርዓት፣

ለ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ ደረጃ ጋር ወይም ባይቀጣ ኖሮ ሊደርስበት ከሚችለው ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ ደረጃ ካልተገኘ ክፍት የሥራ ደረጃው በተገኘ ጊዜ ያለምንም ተጨማሪ የሹመት ሥነ-ሥርዓት፣ በሥራ ደረጃው ላይ እንዲመደብ ይደረጋል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሐ" የተዘረዘሩት ቅጣቶች ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች ሲሆኑ ከፊደል ተራ "መ" እስከ "ረ" የተዘረዘሩት ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች ናቸው።

፭/ አንድ ዐቃቤ ሕግ በዲሲፕሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይና ሊጠቀስበት የሚችለው፡-

ሀ) ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለ፪ (ሁለት) ዓመት፣

ለ) ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለ፭ (አምስት) ዓመት ይሆናል።

e) down grading of one grade for the period of two (2) consecutive years; or prohibitions of one grade promotion from the appointment date for two (2) consecutive years;

f) dismissal.

3/ A public prosecutor who has been taking disciplinary measures in down grading under Sub-article (1) (e) of this Article, after the penalty shall;

a) get the former work grade held or work grade to be reach if there is open similar grade without any appointment procedures;

b) get the former work grade held or work grade to be reach when it is available if there is no open similar grade without any appointment procedures;

4/ Disciplinary penalties enumerated under sub-Article (2) (a) to (c) of this Article are simple disciplinary penalties while those enumerated under (d) to (f) are serious disciplinary penalties.

5/ After a disciplinary measure has been taken on a public prosecutor, such measure shall remain in his record:

a) for 2 (two) years, where the penalty is simple;

b) for 5 (five) years, where the penalty is rigorous.

https://chilot.me


፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ የተደነገገው ቢኖርም በዲሲፕሊን የተቀጣ ዐቃቤ ሕግ በሥራው የላቀ አፈጻጸም ያስመዘገበ ወይም በሕዝባዊ ወይም በማሕበራዊ አገልግሎት መስክ የሚያመሰግን ልዩ አስተዋጽኦ ያበረከተ እንደሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በማንኛውም ጊዜ ምክንያቱን በጽሑፍ ገልጾ የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርዱ እንዲነሳ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤ ትእዛዙም በዐቃቤ ሕጉ የግል ማህደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ አለበት።

**፹፰.የዲሲፕሊን ክስ የማየት ሥልጣን**

፩/ ማናቸውም የዲሲፕሊን ጥፋት በዚህ ደንብ በተወሰነው የአፈፃፀም ሥነ ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ተጣርቶ መፈፀሙ ከተረጋገጠ በዋና ጉባኤው ወይም በንኡስ ጉባኤው ውሳኔ ይሰጥበታል::

፪/ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የሚታየው በዋና ጉባኤው ይሆናል።

፫/ በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የሚታየው በንዑስ ጉባኤው ይሆናል።

፬/ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ለዋና ጉባኤው የቀረበ ክስ ሲጣራ በቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ ከተገኘ ዋና ጉባኤው ራሱ ሊወስን ወይም ወደ ንዑስ ጉባኤ ሊመልሰው ይችላል።

፭/ በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ለንኡስ ጉባኤ የቀረበ ክስ በከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ ለዋና ጉባኤው መተላለፍ አለበት።

**፹፱.በዲሲፒሊን ጥፋት የተከሰሰን ዐቃቤ ሕግ ከሥራ አግዶ ስለማቆየት**

፩/ ማንኛውንም ዐቃቤ ሕግ፡-

ሀ) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክላል፣

6/ Notwithstanding to the provisions of Sub-article (5) of this Article, the Attorney General may give order at any time to take away the disciplinary measures in writing mentioning the reasons when a public prosecutor who has been takeing disciplinary measures had registered best efficiency; or special participation in public or social services; and, the order shall be kept in personal record of the public prosecutor.

**88. Power to Decide Disciplinary Offenses**

1/ Any breach of discipline shall be decided by a Higher or Lower Commission in accordance with the procedure laid down in this Regulation after having been properly investigated.

2/ Rigorous disciplinary offense shall proceed by a Higher Commission.

3/ Simple disciplinary offense shall proceed by a Lower Commission.

4/ Rigorous disciplinary offense after it is known that it is simple disciplinary offense in the investigation shall proceed by a Higher Commission or may return to Lower Commission.

5/ Simple disciplinary offense after it is known that it is rigorous disciplinary offense in the investigation shall be transfered to a Higher Commission.

**89. Suspension from Duty of a Public Prosecutor Accused of Disciplinary Offense.**

1/ Any Public Prosecutor will be suspended from duty if it is presumed that:

a) he may obstruct the investigation by concealing, damaging or destroying evidence related to the alleged offence; or,

https://chilot.me


ለ) በመንግሥት ንብረት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ያደርሳል፣

ሐ) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንጻር የሌሎችን ሠራተኞች ሞራል የሚነካ ወይም ተገልጋዩ ሕዝብ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሊኖረው የሚገባውን እምነት ያዛባል፣ ወይም

መ) ተፈጸመ የሚባለው ጥፋት ከሥራ ያስወጣል ተብሎ ሲገመት ከ ፵፭ (አርባ አምስት) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በሚመለከተው ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሚፃፍ ደብዳቤ የወር ደመወዙ ፷ በመቶ እየተከፈለው ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ ይደረጋል።

፪/ የእገዳ ደብዳቤው፡-

ሀ) ለተከሳሹ በአካል ይሰጠዋል፣

ለ) ተከሳሹ በአካል ካልተገኘ ወይም አድራሻው ካልታወቀ የእገዳው ደብዳቤ በሚሠራበት ቦታ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለ፲ (አሥር) ቀን ተለጥፎ መቆየት አለበት።

፫/ ዐቃቤ ሕጉ በታገደ በ፭ (አምስት) የሥራ ቀን ውስጥ ጉዳዩ ለዋናው ጉባኤ ወይም ለንኡስ ጉባኤ መቅረብ አለበት።

፬/ በተከሰሰበት የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ዐቃቤ ሕጉን ከሥራ የማያሰናበተው ሆኖ ሲገኝ በዐቃቤ ሕጉ ላይ ከሥራ ማሰናበት ያነሰ ቅጣት ቢወሰንበትም ባይወሰንበትም ከሥራ ታግዶ በቆየበት ጊዜ የተያዘበት ደመወዙ ያለወለድ ይከፈለዋል።

፭/ የእገዳው ሁኔታና ዓላማ የግድ ከሚጠይቀው ወይም ከሚያስከትለው ክልከላ በስተቀር በእገዳው ጊዜ የዐቃቤ ሕጉ ሌሎች መብቶችና ግዴታዎች የተከበሩ ናቸው።

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ቢኖርም ከሥራና ደመወዝ ታግዶ የቆየ ዐቃቤ ሕግ ከሥራ እንዲሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ

b) he may commit additional offence on the property of the government institution; or,

c) the alleged offence is so grave as to demoralize other civil servants or negatively affect the public trust towards;

d) the disciplinary offence may lead to dismissal; and, he shall be suspended by a written order of the respective Deputy Attorney General for the period of suspension not exceeding 45 days with 60 percent payment of his salary.

2/ The suspension letter:

a) shall be informed in writing of the reasons for suspension;

b) in the case of the suspended public prosecutor absence or his address is unknown the suspension letter shall be affixed on the notice board of the Office for ten (10) days.

3/ The case shall be lodged for Higher Commission or Lower Commission having jurisdiction within five (5) working days of the suspension of the public prosecutor.

4/ Where the alleged breach of discipline does not entail dismissal, the partially or fully withheld salary shall be paid to the concerned public prosecutor without interest, whether or not a lesser penalty has been imposed on him.

5/ The rights and duties of the public prosecutor remain unaffected by the suspension with the exception of such duties and resistant with conditions and aims of the suspension.

6/ Notwithstanding Sub-article (1) of this Article or in accordance with sub-article (4) of this Article, where it is impossible to examine and decide the case with in

https://chilot.me


፬ መሠረት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ የዕግዱ ጊዜ ካበቃ፡-

ሀ) የመዘግየቱ ምክንያት የዲስፕሊን ክሱን የማጣራቱ ሂደት ውስብስብነት ከሆነ የወር ደመወዙ ፷ በመቶ እየተከፈለው ወይም

ለ) ለመዘግየቱ ምክንያት የሆነው ዐቃቤ ሕጉ ራሱ ከሆነ ያለምንም ደመወዝ ክፍያ፣

በዋና ጉባኤው ጥያቄ እግዱ እስከ አንድ ወር ድረስ እንዲራዘም በሚመለከተው ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሊወሰን ይችላል።

፯/ ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የቆየ ዐቃቤ ሕግ እንዲሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ መደበኛውም ሆነ የተራዘመው የዕግድ ጊዜ ከተጠናቀቀ የሥራና የደመወዝ እግዱ ተነስቶ የዲስፕሊን ክሱ መታየት ይቀጥላል፤ ሆኖም ለመዘግየቱ ምክንያት የሆኑ የዋና ጉባኤ አባላትና የሥራ ኃላፊዎች በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናሉ።

**፺.<u>ስለ ይርጋ ጊዜ</u>**

የሕመም ፈቃድን፣ ብሔራዊ በዓላትን፣ የወሊድ ፈቃድንና በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው የሚውሉበትን ቀን ሳይጨምር፡-

፩/ ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ ዐቃቤ ሕግ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር በዲስፕሊን ጥፋት ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፤

፪/ በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ ዐቃቤ ሕግ የወንጀሉን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም።

the time limit of suspension:

a) where it is impossible to examine and decide the case within the time limit due to the complexity of the case with 60 percent payment of his salary; or

b) where the dalliance is the concerned public prosecutor is himself without any salary payment;

the respective Deputy Attorney General may extend the period of the suspension for up to one month upon the request of the Higher Commission.

7/ Where it is impossible to examine and decide the case within the time limit indicated under Sub-article (4) of this Article, after removal of the suspension of salary and duty the case shall continue to be heard in disciplinary charge. However, members of the Higher Commission and Officials being a cause for dalliance shall be accountable for rigorous disciplinary offences.

**90. <u>Period of Limitation</u>**

Excluding date of sick leave, national holidays, and maternity leave and office day off with government decision;

1/ Disciplinary measure shall not be taken against a public prosecutor who has committed an offence entailing simple disciplinary penalty unless such measure is taken within six months, from the time the commission of the offence is known;

2/ No disciplinary charge shall be brought against a public prosecutor who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty in addition to criminal liability, unless the disciplinary charge is brought within the time limit provided for in the criminal code for such criminal offence.

፫/ በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ ዐቃቤ ሕግ የደንብ መተላለፍ ክስን ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፕሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም።

፬/ የዲሲፕሊን ቅጣት ውሳኔው፡-

ሀ) ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ከሆነ በአንድ አመት፤

ለ) ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ከሆነ በሁለት አመት ውስጥ ካልተፈጸመ በይርጋ ቀሪ ይሆናል።

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

**ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ማጣራትና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

**፺፩.ክስ ስለማቅረብ**

፩/ በዐቃቤ ሕግ የዲሲፕሊን ጥፋት ሲፈጸም ክስ ለዋና ጉባኤው ወይም ለንኡስ ጉባኤው የሚቀርበው በዐቃቤ ሕጉ የቅርብ ሃላፊ ነው።

፪/ የዐቃቤ ሕጉ የቅርብ ሃላፊ በዐቃቤ ሕግ ላይ የሚፈጽመው የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ ለዋና ጉባኤው ወይም ለንዑስ ጉባኤው የሚቀርበው በሕግ ኦዲት ቅሬታና ሥነ ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ነው።

**፺፪.ስለክስ ጽሑፍ**

፩/ ክስ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ ለቀረበበት ክስ በራሱ ወይም በጠበቃው መልስና መከላከያ ለማቅረብ እንዲችል የቀረበበት ክስ የወንጀል ክስ በሚቀርብበት ዝርዝር ሁኔታ የተዘጋጀ ሆኖ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃና መልስ የሚሠጥበትን ቀን፣ሰዓትና ቦታ ከሚገልጽ መጥሪያ ጋር ከ፲ (አሥር) ቀን ቀድሞ እንዲደርሰው መደረግ አለበት።

፪/ ክስ የቀረበበት ዐቃቤ ሕግ ለዋና ጉባኤው ወይም ለንኡስ ጉባኤው መልሱን በጽሑፍ ወይም በቃል

3/ No disciplinary charge shall be brought against a public prosecutor who has committed an offense entailing rigorous disciplinary penalty, but not entail criminal liability, unless the disciplinary charge is brought within the time limit provided for in the criminal code for petty offences.

4/ If disciplinary measures has not committed;

a) within one year for simple disciplinary penalty;

b) within two (2) years for rigorous disciplinary penalty;

shall be barred by limitation.

**Section Three**

**Disciplinary Procedures, Lodging of charges Investigation and Decision**

**91. Lodging of Charges**

1/ Where a disciplinary offense is committed by a public prosecutor, the chargeshall be lodged to thehigher or Lower Commission by the public prosecutor’s immediate superior.

2/ Where a disciplinary offense is committed by a public prosecutor’s immediate superior, the charge shall be lodged to the higher or Lower Commission by the Legal Audit and Inspection Directorate.

**92. Charge Sheet**

1/ Where a public prosecutor is charged with a disciplinary offense, he shall be provided with a charge sheet containing all facts which constitute the breach of discipline, the evidence brought to prove the case together with summons which indicates the date,time and place where he or his advocate presents defense prior to ten (10) days.

2/ A charged public prosecutor may present his defense in oral or written to the higher commission or lower

https://chilot.me


ማቅረብ ይችላል።

፫/ የተከሳሹ ዐቃቤ ሕግ አድራሻ ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት የክሱን ጽሑፍ ወይም መጥሪያ ለተከሳሽ በአድራሻው መላክ ካልተቻለ ዐቃቤ ሕጉ የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት መሆኑንና ክሱ የሚሰማበትን ቀን፣ሰዓትና ቦታ የሚገልጽ ማስታወቂያ ተከሳሹ በሚሠራበት የመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ለ፲፭ (አሥራ አምስት) ቀን እንዲቆይ መደረግ ይኖርበታል።

**፺፫.<u>የቀረበውን ክስ ስለማጣራት</u>**

፩/ ዋና ጉባኤው ወይም ንዑስ ጉባኤው የቀረበለትን የዲሲፕሊን ክስ ለማጣራት በሕግ መሠረት ማስረጃዎችን ያሰባስባል፤ አስፈላጊውን ጉዳይ በተገቢ መንገድ በማጣራት ከተገቢ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲችል በዲሲፕሊን የተከሰሰው ዐቃቤ ሕግና መሥሪያ ቤቱ እያንዳንዳቸው በሚገባ እንዲያስረዱ ማድረግ አለበት።

፪/ ዐቃቤ ሕጉ ጉዳዩ በግልጽ ችሎት እንዲታይለት ካልጠየቀ በቀር የዲስፐሊን ጉዳይ የሚታየው በዝግ ችሎት ነው።

**፺፬.<u>ስለ ውሳኔ</u>**

፩/ በዐቃቤ ሕጉ ላይ የቀረበው የዲሲፕሊን ክስ በዋና ጉባዔው ወይም በንኡስ ጉባኤው ከተጣራ በኋላ፦

ሀ) ዐቃቤ ሕጉ የክስ ጽሑፍ ደርሶት ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፺፪(፫) በተመለከተው መሠረት ተጠርቶ ካልቀረበ ዋና ጉባኤው ወይም ንዑስ ጉባኤው ዐቃቤ ሕጉ በሌለበት ክሱን መርምሮ ይወስናል።

ለ) ዐቃቤ ሕጉን በጥፋተኝነት የማያስጠይቀው ከሆነ ወይም የተከሰሰበት ጥፋት በማስረጃ ካልተረጋገጠ ክሱ ይዘጋል፣

ሐ) የቀረበው ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፯ (፩) የተደነገጉትን መስፈርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ቅጣት ይወስናል።

commission.

3/ Where it is not possible to deliver the charge sheet or summons to the public prosecutor or his address where about is not known to send, the summons indicating the charge brought against the public prosecutors the date, time and place of the hearing shall be affixed on the notice board of the Office where the concerned public prosecutor is working for fifteen (15) days.

**93. <u>Investigation of the charge</u>**

1/ For purposes of investigating disciplinary charges, the Higher or Lower Commission shall, in accordance with law establish facts, collect evidences and apply the necessary procedure. In order for the Commission to arrive at appropriate decision proposal, it shall give proper hearing to both the public prosecutor's charge and the Office who brought the charge.

2/ Unless a public prosecutor request open hearing, disciplinary cases shall be heard in exclusion of the general Public.

**94. <u>Decision</u>**

1/ The Higher or Lower Commission having jurisdiction over the charge brought against the public prosecutor, after proper examination,shall:

a) decide with absence of the public prosecutor when the public prosecutor is absent after he received the charge in writing or could not present in accordance with Article 92(3) of this Regulation;

b) dismiss the charge where the charge could not be established or there was no sufficient evidence to justify conviction;

c) impose disciplinary penalty by taking in to consideration measures listed under Article 87(1) of this Regulation.

https://chilot.me



፪/ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) መሠረት ቀርቦ ለመከራከር ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ምክንያቱ ከተወገደበት ቀን አንስቶ ባለው ፲፭(አሥራ አምስት ቀን ውስጥ) ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ያልቀረበበትን ምክንያት ከሚገልጽ ማስረጃ ጋር በጽሁፍ ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት።

፫/ ዋና ጉባኤው ወይም ንኡስ ጉባኤው የቀረበለት ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው በ፲(አሥር) ቀን ውስጥ ክሱ እንዲታይ መወሰን አለበት።

፬/ በማንኛውም ፈቃድ፣ በብሔራዊ በዓላት ወይም በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውሉበት ቀን የዲሲፕሊን ቅጣት አይጣልም።

## ንዑስ ክፍል አራት

## ስለይግባኝ

### ፺፭.የይግባኝ መብት

፩/ ዋና ጉባኤው ወይም ንኡስ ጉባኤው በሠጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታይለት በ፴ (ሠላሳ) ቀን ውስጥ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ማቅረብ ይችላል።

፪/ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ይግባኝ ባይ ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ የሚቃወምበትን ምክንያት በዝርዝር በየጭብጡ በመለየትና እንዲቀየርለት ወይም እንዲሻሻልለት የሚፈልገውን ጉዳይ በግልጽ ማመልከት አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የቀረበ የይግባኝ ማመልከቻ ለሌላኛው ተከራካሪ ወገን እንዲደርሰው መደረግ አለበት።

፬/በቅርብ ኃላፊው ይግባኝ ቀርቦ የዐቃቤ ሕጉ አድራሻ ባለመታወቁ ወይም በሌላ ምክንያት የይግባኝ አቤቱታውን ለዐቃቤ ሕጉ መስጠት ያልተቻለ እንደሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፺፪(፫) የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ ይግባኝ እንዲታይ የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ወይም በዚህ ደንብ

2/ If the public prosecutor could not present for litigation with in cases of forced measure in accordance with Sub-article (1) of this Article, written request shall be lodged with in fifteen days including with enough reason after the forced measure.

3/ If the reason is accepted by the Higher Commission or Lower Commission, it shall be decided to hear the charge within ten (10) days.

4/ Disciplinary penalties shall not be imposed in national holidays or office day off with government decision except annual leave.

## Section Four

## Appeal

### 95. Right to Appeal

1/ An appeal may be filed against the decision of theHigher or Lower Commission to the Attorney General within thirty (30) days.

2/ The memorandum of appeal shall show in detail and under distinct headings the grounds of objection the decision appealed against and shall state clearly the nature of the relief sought.

3/ An appeal lodged in accordance with Sub-article (2) of this Article shall submit to other party.

4/ Article 92(3) of this Regulation shall be applicable if an appeal lodged by superior could not be submited for public prosecutor due to unknown address or any other reason.

5/ for an appeal filed out of time inconsistent with Sub-article (1) of this Article or an appeal decision provided in absence of the public prosecutor in accordance with

https://chilot.me



አንቀጽ ፺፮(፩) መሠረት በሌለበት የተሰጠ የይግባኝ ውሳኔ እንደገና እንዲታይ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሑፍ ሆኖ ያልቀረበበትን ምክንያት ከሚገልጽ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፮/ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የቀረበለት ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው በ፲ (አሥር) ቀን ውስጥ ይግባኙ እንዲቀርብ ውሳኔ ይሰጣል።

## ፺፮.ስለይግባኝ ውሳኔ

፩/ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፺፭ (፫) መሠረት የይግባኝ ማመልከቻው ደርሶት ካልቀረበ ወይም በዚህ ደንብ ፺፭(፬) መሠረት ተጠርቶ ካልቀረበ በሌለበት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ውሳኔ ይሰጣል።

፪/ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የቀረበለትን የይግባኝ ማመልከቻ መርምሮ የዋና ጉባኤውን ወይም የንዑስ ጉባዔውን ውሳኔ ሊያጸናው ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል።

፫/ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት በይግባኙ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፬/ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ በይግባኙ ላይ በሠጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ዐቃቤ ሕግ በሕግ ጉዳይ ላይ ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

## ፺፯.ስለወጪዎች

የዲሲፕሊን ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ምስክር፣ የሙያ ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ በማቅረብ ረገድ የሚያወጣውን ወጭ ማስረጃ እንዲታይለት ወይም እንዲሰማለት የሚጠይቀው ወገን መክፈል አለበት። ሆኖም ዐቃቤ ሕጉ በቀረበበት የዲሲፕሊን ክስ ጥፋተኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ያወጣው ወጭ በመሥሪያ ቤቱ ይተካለታል።

Article 96(1) of this Regulation, written request shall be lodged including with sufficient ground.

6/ If the reason is acceptede d by the Attorney General, he shall decide to lodge the appeal within ten (10) days.

## 96. Decision of Appeal

1/ The Attorney General shall provide decision where the public prosecutor is absent in accordance with Article 95(3) of this Regulation after receiving the memorandum of the appeal or due to summons in accordance with Article 95(4) of this Regulation.

2/ The Attorney General may ratify, amend or repeal the decisions of the Higher or Lower Commission.

3/ The decision of the Attorney General in accordance with Sub-article (2) of this Article shall be final.

4/ A public prosecutor who has grievance against the appeal decision of the Attorney General may lodge an appeal to High court to issues related with law.

## 97. Expenses

The expenses concerning witnesses, professional witnesses or other evidences brought before the disciplinary hearing shall be borne by the party who brought them. However, the expenses shall be reimbursed to the public prosecutor by the Office where he is found not-guilty of the disciplinarycharge.

https://chilot.me


## ክፍል ስምንት

## ስለ ዋና ጉባኤና ስለንኡስ ጉባኤ

**፺፰.የዋና ጉባኤው አባላት**

፩/ የዋና ጉባኤው አባላት ሆነው የሚሰየሙ ዐቃብያነ ሕግ በሥራ ልምዳቸው፣ በሕግ ዕውቀታቸው፣ በከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤታቸው፣ በታታሪነታቸው፣በታማኝነታቸው፣በፍትሐዊነታቸውና በሥነ-ምግባራቸው መልካም ስም ያተረፉና በሥራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚታመንባቸው ሆነው፡-

ሀ) በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የሚሰየሙ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ረዳት ጠቅላይ ዐቃብያነ ሕግ፣

ለ) በዐቃብያነ ሕግ የሚመረጡ ሁለት ምክትል ረዳት ጠቅላይ ዐቃብያነ ሕግና አንድ ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ አባላት፤

ሐ) የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ድምጽ የማይኖረው ጸሐፊ

ይኖሩታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከሚመረጡት የዋና ጉባኤ አባላት መካከል ቢያንስ አንዱ ዐቃቢተ ሕግ መሆን አለባት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሐ) ከተደነገገው በስተቀር የዋና ጉባኤውአባላት፡-

ሀ) የሥራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል።

ለ) ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ሊያገለግሉ አይችሉም።

**፺፱.የዋና ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

ዋና ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የዐቃብያነ ሕግን ቅጥር፣ ሹመት፣ ዝውውር ወይም ድልድልን በሚመለከት ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

፪/ የዐቃብያነ ሕግን የሥራ ኃላፊነት ደረጃን እንደገና የመመደብን፣ ድርጅታዊ መዋቅርን፣

## PART EIGHT

## Higher Commission and Lower Commission

**98. Members of the Higher Commission**

1/ Public prosecutors designated as members of the Higher Commission shall have good reputation for their legal knowledge and experience, for their efficiency, diligence, integrity, sense of justice, good conduct and for having won the confidence of their colleagues and the Commission shall have the following:

a) chair person and vice Chairperson Assistant Attorney General designated by the Attorney General;

b) two deputyAssistant Attorney Generals, members selected by public prosecutors; and,

c) one head Office of a Public Prosecutor Administration councilwithout vote.

2/ In accordance with Sub-article (1) of this Article among members of the higher Commission shall be a female public prosecutor.

3/ Unless Members of the Higher Commission stated in accordance with Sub-article (1)(c), of this Article:

a) shall have a two years term of office;

b) shall not serve more than a two years term of office;

**99. Powers and Responsibility of theHigher Commission**

The Higher Commission shall have the following powers and responsibilities:

1/ to recommend to the Attorney General the employment transfer and appointment or deployment of public prosecutors.

2/ to study or cause to be studied and make recommendations to the Attorney General on matters

https://chilot.me


የደመወዝ ስኬልን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማድረግ ወይም በማስጠናት ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል። ሲጸድቁም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል።

፫/ ይህን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓቶችን፣ መመዘኛዎችንና ቅፆችን እያዘጋጀ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ያቀርባል፣ሲጸድቁም አፈፃፀማቸውን ይከታተላ።

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፪ መሠረት በአንድ ዐቃቤ ሕግ ላይ በሚደረስ የችሎታ ማነስ ዘገባ ላይ ስለሚወሰደው እርምጃ የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ያቀርባል።

፭/ በዚህ ደንብ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የዲሲፕሊን ጉዳዮችን መርምሮ ይወስናል።

፮/ በዚህ ደንብ የተሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**፻. ስለንዑስ ጉባኤ መቋቋም**

በዋናው መሥሪያ ቤትና የመሥሪያ ቤቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በሚገኙባቸው ክልሎች የዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ንኡስ ጉባኤ እንደአስፈላጊነቱ ይቋቋማል።

**፻፩.የንዑስ ጉባኤው አባላት**

፩/ የንዑስ ጉባኤው አባላት ሆነው የሚሰየሙ ዐቃብያነ ሕግ በሥራ ልምዳቸው፣ በሕግ ዕውቀታቸው፣ በከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤታቸው፣ በታታሪነታቸው፣በታማኝነታቸ፣ በፍትሐዊነታቸውና በሥነ-ምግባራቸውመልካም ስም ያተረፉና በሥራ ባልደረቦቻቸው ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚታመንባቸው ሆነው፡-

ሀ) በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚሰየሙ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣

ለ) በዐቃብያነ ሕግ የሚመረጡ ሦስት አባላት ይኖሩታል። የንኡስ ጉባኤው አባላትም ከመካከላቸው ጸሐፊውን ይመርጣሉ።

concerning the organizational structure, re-classification of position and salary scale and follow up their implementation upon approval.

3/ prepare and submit to the Attorney General and follow up their implementation upon approval of guidelines,procedures, criteria and formats as may be necessary for the implementation of this Regulation.

4/ to make recommendations to the Attorney General of the measures to be taken on an inefficiency reports of a public prosecutor submitted in accordance with Article 62 of this Regulation.

5/ to decide disciplinary cases in accordance with the powers conferred to it under this Regulation

6/ to carry out other responsibilities entrusted to it by this Regulation.

**100. Establishment of the Lower Commission**

Public prosecutor administration Lower commission in the Main Head Office and Regional Branch Offices is established as may be necessary.

**101. Members of the Lower Commission**

1/ Public Prosecutors designated as members of the Lower Commission shall have good reputation for their legal knowledge and experience, for their efficiency, diligence, integrity, sense of justice, good conduct and for having won the confidence of their colleagues and the Commission shall have the following:

a) chair person and Vice Chairperson designated by the Attorney General;

b) three members selected by public prosecutors and members of the Lower Commission shall select a secretary.

https://chilot.me


፪/ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የንዑስ ጉባኤው አባል ሆኖ አይሠየምም።

፫/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፺፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተደነገጉት ለንኡስ ጉባኤ አባላትም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2/ Head of the Branch office shall not be designated as a member of lower Commission.

3/ The provisions under Sub-article (2) and (3) of Article 98 shall apply to the Lower Commission.

**፩፻፪.የንዑስ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ንዑስ ጉባኤው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፹፰(፫) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት የዲሲፕሊን ጉዳዮችን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

፪/ በክልሉ ተመድበው እንዲሠሩ በክልሉ ስለሚመለመሉ ዐቃብያነ ሕግ አመራረጥ፣ ቅጥርና ሹመት አስተያየቱን ለዋና ጉባኤው ያቀርባል።

፫/ በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሥር ተመድበው የሚሠሩ ዐቃብያነ ሕግ በያዙት የሥራ ደረጃ በክልሉ ውስጥ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር የሚያቀርቡትን ጥያቄ በመመርመር አስተያየቱን ለዋና ጉባኤው ያቀርባል።

፬/ በዚህ ደንብና በዋና ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**102. Powers and Responsibility of the Lower Commission**

1/ The Lower Commission shall provide final decision for disciplinary cases in accordance with the powers conferred on Article 88 (3) under this Regulation.

2/ To recommend to the higher commission the employment transfer and appointment of public prosecutors selected by the Region.

3/ To recommend to the Higher Commission request of Public Prosecutor transfer assigned in the branch office with the same work grade from one place to the other in the same region.

4/ to carry out other responsibilities entrusted to it by this Regulation and Higher Commission.

**፩፻፫.የዋና ጉባኤውና የንኡስ ጉባኤው የአሠራር ሥነ-ሥርዓት**

የዋና ጉባኤው ወይም የንዑስ ጉባኤው የአሠራር ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፦

፩/ በማናቸውም ስብሰባ ከአባላት ሁለት ሦስተኛ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።

፪/ ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ይወሰናል።

፫/የዋና ጉባኤው ወይም የንኡስ ጉባኤው አባላት ድምጽ እኩል ከሆነ የዋና ጉባኤው ወይም የንኡስ ጉባኤው ሰብሳቢ ያለበት ወገን ውሳኔ የዋና ጉባኤው ወይም የንዑስ ጉባኤው ውሳኔ ይሆናል።

፬/ ዋና ጉባኤው ወይም ንዑስ ጉባኤው በድምጽ ብልጫ በሚወሰንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛው

**103. Rules of Procedures of Higher Commission and Lower Commissions**

The rules of procedures of the Higher Commission and Lower Commission shall be as follows:

1/ There shall be a quorum where two-thirds (2/3) of the members are present at the meetings of the Commission.

2/ All matters shall be decided by a majority vote of the members present.

3/ In case of a tie, the chair-person of the Higher Commission or Lower Commission shall have a casting vote.

4/ Where decisions are taken by a majority vote in the Higher Commission or Lower Commission the dissenting opinion of the minority' shall be recorded.

https://chilot.me



ድምጽ አስተያየት ከነምክንያቱ በስብሰባው ቃለ ጉባኤ መመዝገብ አለበት።

፭/ ማንኛውም የዋና ጉባኤው ወይም የንዑስ ጉባኤው አባል የራሱ፣ የዘመዶቹ ወይም የወዳጆቹ የግል ጉዳይ ወይም ጥቅም ከሥራው ወይም በሥራው ምክንያት ከያዘው የሕዝብ ወይም የግለሰብ ጉዳይ ጋር የሚጋጭ ሆኖ ሲገኝ በስብሰባው ላይ በመገኘት ጉዳዩን መመልከት አይችልም።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት የዋና ጉባኤው ወይም የንኡስ ጉባኤው አባል በመነሳቱ ምክንያት ምልዐተ ጉባኤው መሟላት የማይችል ከሆነ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ጊዜያዊ የዋና ጉባኤው ወይም የንዑስ ጉባኤው አባል ሊመድብ ይችላል።

፯/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ዋና ጉባኤው ወይም ንኡስ ጉባኤው የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፻፬.ስለ ሙያ ተለማማጅ

ስለ ሙያ ተለማማጆች ቅበላና የተግባር ልምምድ ስለሚያደርጉበት ዝርዝር ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

### ፻፭.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በፌደራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፺፩ መሠረት በዋና ጉባኤው በመታየት ላይ ያሉ የዲሲፕሊን ጉዳዮች በተጀመሩበት መንገድ ውሳኔ ያገኛሉ።

### ፻፮.የተሻሩ ሕጎች

፩/ የፌደራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፬/፲፱፻፺፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

5/ Any members of the Higher Commission or Lower Commission, when private case or benefits of his relatives or friends inconsistent with his duties or public or private issues shall not be present at the meeting and see the case.

6/ In accordance with Sub-article (5) of this Article, members of the Higher Commission or Lower Commission is incomplete, the Attorney General may assign temporary members of Higher or Lower Commission.

7/ Where necessary the Higher Commission or Lower Commission may, without prejudice to the provisions of this Article, draw up their own rules of procedure.

## PART NINE
## Miscellaneous Provisions

### 104. Apparent ship Trainers

Details of acceptance and practice of apparent ship trainee shall be determined by a directive.

### 105. Transitory Provision

Pending disciplinary cases by the Higher Commission pursuant to former Regulation shall continue to be heard in Federal Prosecutor Administration Council of Ministers Regulation No.44/1997.

### 106. Repealed Laws

1/ Federal Prosecutor Administration Council of Ministers Regulation No. 44/1997 is hereby repealed by this Regulation.

2/ No law, regulation, directive or practice inconsistent with the provisions of this Regulation shall apply to matters covered under this Regulation.

https://chilot.me



**፩፻፯.** **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ዶ/ር አቢይ አሕመድ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**107. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the dateof publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of December, 2018.**

**ABIY AHMED (DR)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**